# ድህነት-ተኮር አገልግሎቶች በኢትዮጵያ

## የዜጎች አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ
## (የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት)

በፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ
ኢን ኢትዮጵያ(ፓአኔኢ) የተዘጋጀ

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1998 ዓ.ም.

**ማውጫ**

**መቅድም**
**ምሕፃረ ቃላት**

**ገጽ**


**1. መግቢያ ........................................................................................ 6**
1.1. የዜአካ ምንድን ነው?........................................................... 6
1.2. ፓአኤኢ ............................................................................. 9
1.3. የዜአካ በኢትዮጵያ.............................................................. 10
1.4. የሙከራ ጥናቱ ንድፍ............................................................ 11
1.5. የጥናቱ ዘዴ........................................................................ 12
1.6. የጥናቱን የትኩረት ነጥቦችሐሃሳቦችን መለየት........................ 12
1.7. የጥናቱ ውሱንነት................................................................ 15
**2. የጥናቱ ናሙና ቤተሰቦች ማሕበራዊና ስነ ህዝባዊ ገጽታ ................ 16**
2.1. የትምህርት አሠጣጥና ትምህርት.............................................. 16
2.2. የጋብቻ ሁኔታ...................................................................... 17
2.3. የሥራ ሁኔታ........................................................................ 17
2.4. የመገልገያ አቅርቦት ............................................................. 17
**3. ማጠቃለያና የፖሊሲ ጠቋሚዎች ..................................................... 18**
3.1. የመጠጥ ውሃ ዘርፍ ............................................................... 18
3.2. የጤናና የንፅህና አገልግሎት ሁኔታ.......................................... 20
3.3. ትምህርት ............................................................................ 22
3.4. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት........................................... 23

**4. ዘርፎችና ክልሎች እንዴት ይለካሉ? .................................................. 25**
4.1. የግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን ዕድል ማግኘት....................... 25
4.2. ከህዝብ የአገልግሎት ተቋማት ግልጋሎትን የመጠቀም ሁኔታ.. 25
4.3. የህዝብ ግልጋሎቶች ጥራት/አስተማማኝነት.................................. 26
4.4. በመንግስት አገልግሎቶች የመርካት ሁኔታ ................................ 27

**አባሪዎች ....................................................................................... 28-35**


ከሰንጠረዥ 2 እስከ 9

## መቅደም

ይህ ሪፖርት የያዘው በኢትዮጵያ ቀዳሚና ወሣኝ በሆኑ የሕዝብ አገልግሎቶች አሠጣጥ ሁኔታ ላይ የተደረገውን ጥናት ግኝቶች ነው፡፡ ጥናቱ የሚያጠነጥነው በአገልግሎት ተጠቃሚ አስተያየት ፅንሰ-ሀሣብ ላይ በመሆኑ የሕዝብ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ዜጐች የአገልግሎቶች ተጠቃሚነት ዕድል በሚያገኙበትና አገልግሎቶችን በሚጠቀሙበት ወቅት ስላለው ሁኔታ የሠጡትን አስተያየትና ያጋጠማቸውን ተሞክሮዎች ይዘረዝራል፡፡ እዚህ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ጥንቃቄ ሊወሠድበት የሚገባውና ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር የዚህ ጥናት ዋና ፍላጐት በጥናቱ በተገኙ ጉድለቶች ላይ ተመሥርቶ ጣት ለመቀሰር ወይንም በግልጋሎት አሠጣጥ ላይ ቅሬታ ለማቅረብ አይደለም፡፡ ይልቁንም ጥናቱ በዋነኛነት የተፈለገው ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ እንደዋለው እንደ የዜጐች አስተያየት መሠብሠቢያ ካርድ /ዜአካ/ የመሳሠሉት ዘዴዎች በአግልግሎት አሠጣጥ ረገድ የሚፈጠሩ ጉድለቶችንና መንስኤዎቻቸውን ፈልፍሎ ለማወቅ ጠ ቃሚ እንደሆነ ታውቆ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ተቋማት ይህንኑ ዘዴ ተጠቅመው የአገልግሎታቸውን ሽፋንና ጥራት ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት ለመደገፍ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በተለይ ኢትዮጵያ የተለያዩ የፓሊሲ ማሻሻያዎችን እያደረገች ባለችበት በአሁኑ ወቅት ከእንደነዚህ ያሉ ጥናቶች የሚገኙ ጠቋሚዎች በእርግጠ ኝነት መንግሥትን ከተጠቃሚው ሕዝብ ጋር በቅርበት ተገናኝቶ እንዲሠራ ከመርዳታቸውም በላይ ችግርን በጋራ ተነጋግሮ መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡

በተጨማሪም ፓአኔኢ የዚህ ጥናት ግኝቶችና የፓሊሲ ጠቋሚዎች የሁለተኛውን የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሣ ማለትም ድህነትን ለማስወገድ የፈጣን ዕድገትና ዘላቂ ልማት ዕቅድን/ድማፈዘልዕ/ በአግባቡ ለመተግበር ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉና የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሣ ፕሮግራም /ድማፈዘልዕ/ ሂደትን ለማወቅ ለሚቀርበው አመታዊ የተግባር አፈፃፀም ሂደት ሪፓርት (APR) ጥሩ እይታ እንደሚሠጡ ያምናል፡፡ ምንም እንኳን ይህ አመታዊ የተግባር አፈፃፀም ሂደት ሪፓርት (APR) የተነደፈው በዋነኛነት ከአገልግሎት ሠጪው አንፃር ያሉ አመላካቾችንና ቁልፍ ጠቋሚዎችን ተጠቅሞ የተግባር እርምጃ ሂደትንና በጊዜ ሰሌዳ መሠረት የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካትና በዚህ ሁኔታ ያሉ ቅሬታዎችን ለማወቅ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ከአገልግሎት ተቀባዩ አንፃር ሊታዩ የሚችሉ ሌሎች አመላካቾችን አሣታፊ የሆነ ዘዴን በመጠቀም ለዚሁ ተግባር ማዋል ድህነትን ለመቀነሥ የተነደፉ ሥልቶችና ማሻሻያዎች በዚሁ አንፃር ያበረከቱትን አሥተዋፅኦና የሥርጭት ሽፋን ለማወቅ የእይታ መነፅርን እንደሚያሰፉ ያለው ግንዛቤና ተቀባይነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ያለ ገፅታ ያላቸው ሌሎች ተጨማሪ መለኪያዎችን መጠቀም ሠፋ ያለ ግንዛቤን ለመጨበጥና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት አጋሮች ችግር ከመፈጠሩ በፊት አስቀድመው ለሚያደርጉት ተሣትፎዎች ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡

እንግዲህ በዚህ ረገድ እንደ የዜጐች አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ ያሉ አሳታፊ ዘዴዎች በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ የተመሰረቱ ተከታታይ የሆኑ፣ በአሃዝ የማይገለፁና በአሃዝ የሚገለፁ የጥናት ውጤቶች ላይ ለመድረስ ያስችላሉ ተብለው የሚጠበቁት፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ሌሎች ተቀባይነት ያላቸውን የጥናት

አካሄዶችንና ዘዴዎችን ተጠቅመው የተደረጉ ጥናቶችን ውጤት እንደሚደግፍ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የዜአካን ዘዴ በመጠቀም የተገኘ የጥናት ውጤት የአገልግሎት ተጠ ቃሚዎችን አሥተያየት መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሕዝብ አገልግሎቶችን አሠጣጥ የጥራት ደረጃ ለመመዘን የሚያሥችል መነሻ በመሆን ሊያገለግል በመቻሉ ፓአኔኢ ተመሣሣይ ጥናቶችን በቀጣይ የማካሄድ ፍላጐት አለው፡፡ ፓአኔኢ ይህንን ሲያደርግ ለቀጣይ እድገትና ድህነት ቅነሣ ፕሮግራም የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ጥረት በሚደረግበት በአሁኑ ወቅት ተጨባጭ በሆነና በአገልግሎት ተጠቃሚዎች በሚሠጥ አስተያየት ላይ ተመሥርቶ የበኩሉን ድርሻ እንደሚያበረክት በማመን ነው፡፡

በመጨረሻም ለተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና ለአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ(Action Aid Ethiopia) ለዚህ ጥናት መሳካት ስላደረጉት የገንዘብና የቴክኒክ እገዛ ፓአኔኢ ልባዊ ምሥጋናውን ለማቅረብ ይወዳል፡፡ በተጨማሪም የፓአኔኢ አባል ለሆኑትና ለዚህ ጥናት መሳካት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ድጋፋቸውን ላበረከቱት ሁሉ ፖአኔኢ ላቅ ያለ ምሥጋናውን ያቀርባል፡፡ በመጨረሻም ይህንን ተቀዳሚነት ያለውን የሙከራ ጥናት እውን በማድረግ ረገድ የሥልጠናና የጥናት ሥራውን ላገዘንና በሕንድ ሀገር ለሚገኘው ፐብሊክ አፌርስ ፋውንዴሽን ለተባለ የቴክኒክ አማካሪ ድርጅት ላቅ ያለ ምሥጋና በፓአኔኢ ስም አቀርባለሁ፡፡

**እሸቱ በቀለ**
**የፓአኔኢ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር**

## ምሕፃረ ቃላት

- → **ዜአካ** - **የዜጐች አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ**
- → **መያድ** - **መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት**
- → **ድህነት ተኮር አገልግሎቶች በኢትዮጵያ** - Pro-Poor Services in Ethiopia
- → **ፓአኔኢ** (PANE)- **ፖቨርቲ አክሽን ኔትዎርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኢን ኢትዮጵያ**
- → **ድቅዘልሰ** - **የድህነት ቅነሳና የዘላቂ ልማት ሰነድ** (PRSP- Poverty Reduction and SustainableDevelopment Paper)
- → **ዘልድቅፐ** - **የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም** (SDPRP- Sustainable Development and Poverty Reduction Program)
- → **ድማፈዘልዕ** - **ድህነትን ለማስወገድ የፈጣንና ዘላቂ ልማት ዕቅድ** (PASDEP- Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty)
- → **የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች** - Millinium Development Goals(MDGs)

# 1.1 መግቢያ

## 1.1 የዜጎች አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ /ዜአካ/ ምንድነው?

የዜጎች የአገልግሎት እርካታ አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ /ዜአካ/ በቀላሉ ተግባር ላይ የሚውል ነገር ግን ለነዚህ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑ ሰዎች ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ የሚያስችል በቂ አቅም ያለው ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ከናሙና ዳሰሳ ጥናት ጋር ተጣምሮ በመጠቀም ስለአገልግሎት ጥራት የበለጠ ግንዛቤ ካላቸው የአገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚሰጧቸውን አስተያየቶች የሚቃኝ ሲሆን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚሰጠ ት አገልግሎት ረገድ ያሏቸውን ደካማና ጠንካራ ጐን ለመለየት ያስችላቸዋል፡፡

በዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም ረገድ ዜአካ በተጨባጭ ከአገልገሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ጀምሮ እስከ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ድረስ ከታች ወደላይ ያለውን የአንድን የተለየ በሥራ ላይ የዋለ የአገልግሎት ማሻሻያ እርምጃን ሽፋንና ያስገኘውን ጥቅሞች በመቃኘት ተጨባጭ የሆነ መረጃን ለማስገኘት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ዜአካ ዜጐች (በተለይም ደሀውና በቂ አገልግሎት የማያገኘው የሕብረተሰብ ክፍል) የአገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን እድል ለማግኘት በሚጥሩበት ጊዜ የሚያጋጥማቸውን እንቅፋት ለመለየት ከማስቻሉም በላይ የአገልግሎቶችን ጥራት ደረጃ ለመወሰን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሰራተኞችን የሥራ ውጤታማነት ለማወቅ ያስችላል፡፡ በዜአካ አማካኝነት የተገኙ እይታዎችም በተግባር ላይ ይውላሉ ወይንም ለሚውሉ የዘርፍ ፓሊሲዎችና፣ የመርሀ ግብር ስልቶች በአገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ረገድ ያሉ ችግሮችን በአግባቡ ተገንዝበው አስፈላጊውን ምክርና አስተያየት በመስጠት የተስተዋሉ እንቅፋቶችን አስወግዶ የአገልግሎቶችን አሰጣጥ ሽፋንና ጥራት ለማሻሻል ይረዳሉ፡፡

የዜአካ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የተለያዩ አገልግሎቶች ወይም ፍጆታዎች ተጠቃሚ ለሆኑ ሰዎች እኩል እድል የሚሰጥ የናሙና አወጣጥ ዘዴ (random sampling technique) ተጠቅሞ በመምረጥና የዳሰሳ ጥናትን በማካሄድ ሲሆን፣ በናሙናነት የተወሰዱት የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ስላጋጠማቸው ምክንያቶች የሚሰጡት አስተያየቶች በጥቅሉ ተደምረው የግልጋሎቶችን ደረጃ በመወሰን ነው፡፡ በተጨማሪም ዘዴው በተለያዩ መርሀ ግብሮች የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወደ የጋራ የዘርፍ ጉዳዮች ለመለወጥ ከማገዙም ባሻገር ለከፋ ችግሮች ትኩረት ሰጥቶ ማሻሻያዎችንና የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችላል፡፡ በተያየዘ መልኩ የዜአካ ዘዴ በተለያዩ የአገልግሎቶች ዘርፎች የታየ መልካም ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ ስለአጠቃላይ ሁኔታ ጥቅል የሆነ አስተሳሰብና ችግር አፈታት ዘዴን ለማዳበር ይረዳል፡፡ ዘዴው የአገልግሎቶችን የጥራት ደረጃ ለመወሰን የሚያስችል በመሆኑ እያንዳንዱ የአገልገሎት ተጠቃሚ ከሚያጋጥሙት ችግሮች ባሻገር ተጨማሪ እይታ እንዲኖር ስለሚረዳ በእያንዳንዱ አገልግሎት የሚታየውን አወዛጋቢ ሁኔታ ከሌላ የአገልገሎት መዋቅር እና አሰጣጥ ንዑስ ክፍል አንፃር በመቃኘትና በማወዳደር ስልታዊ የሆነ ጥቅል የአገልግሎት ማሻሻያ መፍትሄን ለመንደፍ ያስችላል፡፡

የዜአካ ዘዴ የዜጐችን በግልጋሎት የመርካት ወይንም ያለመርካት ሁኔታ በመጠ ቆም ያሏቸውን አስተያየቶች በቀላሉ እና በማያምታታ መልኩ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ዘዴው የዜጐችን ጥቅል የአገልገሎት እርካታ አስተያየት ለማቅረብ ከማስቻሉም ባሻገር በእያንዳንዱ አገልግሎት ስላሉና ስለተለዩ የአገልግሎት

ገጽታዎች የተሰጡ አስተያየቶችን ለማወቅ ያስችላል:: ለምሳሌ ያህል አንድ ተገልጋይ ዜጋ የመጠጥ ውሃ አገልግሎትን በተመለከተ ሊሰጥ የሚችለው እጅግ ወሳኝ ነገር ግን ግልፅ የሆነ የማሻሻያ አስተያየት ተጠቃሚው በአገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ስለመርካቱ ሲሆን ይህንንም በዜአካ ዘዴ በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል::

ዘዴው ተገልጋዩ የሰጠውን አስተያየት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያንኑ አስተያየት ሠጪ ሥለዛው ግልጋሎት ሌላ ገጽታ የግምገማ አስተያየቱን እንዲሰጥ ስማድረግ ያስችላል:: በመሆኑም ለምሳሌ በአንድ ያገልግሎት ተጠቃሚ አስተያየት መሠረት የውሃ አቅርቦት መጠን ከውሃ ጥራት የበለጠ መጥፎ ተደርጐ ሊገመግም ይችላል:: ስለዚህ ከዚህ አስተያየት ተነስተን ስንናገር ምንም እንኳን የውሃ አቅርቦት ጥራት ማነስ ተገልጋዩ ሙሉ በሙሉ አልረካሁም ብሎ አስተያየት ለመስጠቱ ምክንያት ቢሆንም፤ ችግሩን በማስወገዱ ረገድ የውሃን መጠን በቂ ማድረግ ቀዳሚ ማስተካከያ እርምጃ ይሆናል ማለት ነው:: ባጠቃላይ ከላይ ከተብራራው መረዳት የሚቻለው በዜአካ ዘዴ መሠረት የአገልግሎት ተጠቃሚዎች እርካታ የሚለካው ነጠላ በሆነ የአገልገሎት ገጽታ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት ብቻ መሰረት አድርጐ ሳይሆን በየአገልግሎቱ ያሉ ከአንድ በላይ በሆኑ ገጽታዎች ላይ የሚሰጠ ውን አስተያየት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው:: ይህም የዜአካ ልዩ መገለጫው ነው::

የዜአካ ዘዴ የተጠቃሚዎችን የአገልግሎት እርካታ ደረጃን በመለካት ብቻ ሳይወሰን በአገለግሎት ሰጪ ተቋማትና በተጠቃሚ ዜጐች መካከል ያሉ የተለያዩ ገጽታዎችን ግንኙነት ለመረዳት ያስችላል:: በመሆኑም በግንኙነቱ ረገድ የሚፈጠ ሩና ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ለይቶ ለማወቅ ያስችላል:: በሌላ አነጋገር ሲገለጽ ከዜአካ ሂደት መረዳት የሚቻለው የተጠቃሚዎች በአገልግሎት ያለመርካት ሁኔታ ከተለያዩ ምክንያቶች ጋር ግንኙነት አሉት:: እሱም፦

ሀ/ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለአገልግሎቱ ጥራት ያላቸውን የእርካታ መጠን (ለምሳሌ እንደ የውሃ አገልግሎት አቅርቦት አስተማማኝነት ወይንም በህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማሪያ መጻሕፍት በበቂ ሁኔታ መሟላት)

ለ/ ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያጋጠሟቸው ችግሮች ከግልጋሎት ሰጭ ተቋማት ጋር በመማከር ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት የሚያጋጥማቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች

ሐ/ ያገልግሎቶችን ጥራት ደረጃ ከፍ ለማድረግ (ለምሳሌ መምህራንን ለማነቃቃት የሚያደርጉት ተጨማሪ ክፍያ ወይንም የውሃ ንጽህናን ለመጠበቅ ሲባል የሚደረግ ኢንቨስትመንት) ከሚያስፈልጉ ወጪዎች ጋር ያለ ግንኙነት ...ወዘተ:: ስለዚህ ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው በዚአካ ዘዴ መሰረት በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል ስለአገልግሎቶች አሰጣጥና ሁኔታ ከተጠቃሚዎች መረጃ የሚሰበሰበው የተለያዩ የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ገጽታዎችን በመዳሰስ ነው::

የዜአካ ጥናቶች አላማ አስተያየትን ለመሰብሰብ ብቻም ተደርጎ መታየት የለበትም:: ከዚህ በተጨማሪ ጥናቶቹ ዜጐች በግልም ሆነ በጋራ ሆነው ወቅታዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚፈልጉበት ወቅት የተለያዩ አማራጮችን ውጤታማነት ለመፈተሽ ያስችላቸዋል (ለምሳሌ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች የሆኑ ዜጐች ተጨማሪ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን

ለማረጋገጥ)። ስለዚህ የዜአካ ዘዴ ዜጐች የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ለማሻሻል ያሏቸውን አማራጮች በሚገባ ለይተው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

ሌላው የዜአካ ዘዴ ዋነኛ ገጽታ ይህንን ዘዴ ተመርኩዘው የተሰሩ ጥናቶች ያሏቸው ከፍተኛ ተአማኒነት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት የጥናቶቹ ድምጻሚዎች ከአንድ አቅጣጫ ብቻ በሚያስቡና በአገልግሎት ላይ ቅሬታ ባላቸው ጥቂት ሰዎች በሚሰጡት አስተያየቶች ላይ ብቻ ያተኮሩ ባለመሆናቸው ነው። በተጨማሪም የዜአካ የናሙና አመራረጥ እኩል እድል የሚሰጥ የናሙና አወጣጥ ዘዴን በመከተል ወደ አንድ ሳያጋድል ከሁሉም አይነት የአገልግሎት ተጠ ቃሚዎች (ለምሳሌ በአገልገሎቱ ከረኩትም ካልረኩትም) ናሙናዎችን ስለሚወስድና የተለያዩ አስተያየቶችን ስለሚያንፀባርቅ በዚህ ዘዴ ላይ ተመርኩዞ የተሰራ የዜጎች የአገልግሎት አስተያየት ጥናት አስተማማኝና ሁሉን-አቀፍ የሆነ የአገልግሎትን አስተያየት የሚያቀርብ መሆኑ ዘዴውን የበለጠ አስተማማኝ እንዲሆን አድርጐታል።

ባጭሩ የዜአካን ዘዴን በመጠቀም የተገኙ የእውቀት ፍንጮች:-

ሀ/ ድሀ-ተኮር የሆኑ አገልግሎቶች በምን ያህል ደረጃ ድሆችን ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ ለማወቅ

ለ/ በአገልግሎት ደረጃና በተገልጋይ ፍላጎት መካከል ያለ ክፍተትን ለማወቅ አገልግሎቶች ፈራቸውን ለቀው እንዴት ሊጠቅሙ ከታሰበው የህብረተሰብ ክፍል ውጪ ወደ ሌላ ሊያዘነብሉ እንደቻሉ (ለምሳሌ ደሀውን ከማገልገል ይልቅ ለሀብታም ተጨማሪ ግልጋሎት መሥጠት) ለማወቅ የሚያስችል ብልጭታን ይሰጣሉ። በተመሳሳይ መልኩ ዘዴው ድሃው የህብረተሰብ ክፍል አገልግሎቶችን ከማግኘትና ከመጠቀም የሚያግዱትን እንቅፋቶች ለመለየት ከማስቻሉም በላይ ተገልጋዮች ችግሮችን ለማስወገድ ይጠቅማሉ ብለው የሞከሯቸውን አስተያየቶች በመሰብሰብና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግርን ለመቅረፍ የሚያስችሉ መፍትሄዎችን ለመለየት ይጠቅማል። በመጨረሻም የዜአካ ዘዴ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ በተደረጉ ጥናቶች የተደረሱ የፓሊሲ ድምጻሚዎች (የአገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎችን አስተያየቶች በመጠቀም) ምን ያህል እውነትነት ወይም ተጨባጭነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

የዜአካ ዘዴ ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የሚኖረውን ጥቅም በምናይበት ጊዜ ዘዴው እነዚሁ ተቋማት በዋነኛ የህዝብና የሌሎች ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን አስተያየቶች በመሰብሰብና በማደራጀት በፓሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር የመንግስት አካላት ከሆኑት የተለያዩ የፖሊሲ አውጪ ተዋናዮች ጋር የአጋርነትና የምክክር ተግባርን ለማዳበር ያስችላቸዋል። በመተሣሣይ መልኩ የዜአካ ዘዴ የሲቪል ማህበረተሰብ ተቋማት ከየራሳቸው ግላዊ አስተያየት ወይንም አመለካከት በመነጨ ለፖሊሲ ጉዳዮች ትኩረት ከመስጠት ወደ እውነተኛና ተጨባጭ አህዝን መሠረት ወደአደረጉ የፓሊሲ ጉዳዮች (አጀንዳዎች) እንዲያተኩሩ የሚያስችላቸውን ትጥቅ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም ዘዴው እነዚህ ተቋማት አገልግሎት ሰጪዎች በምን ሁኔታ ውስጥ ሆነው ስራቸውን እንደሚያከናውኑ ለመረዳት የሚያስችል እውቀት እንዲጨብጡ እድል ከመስጠቱም ሌላ ችግሮችን ለመፍታት ህብረተሰቡ ሊወስዳቸው ለሚገቡ እርምጃዎች የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመፈለግ ይረዳቸዋል።

## 1.2 ፖቨርቲ አክሽን ኔትዎርክ ኢትዮጵያ (ፓአኔኢ)

የዜአካ የሙከራ ጥናት በፓአኔኢ የተደረገ ተቀዳሚነት ያለው ጥረት ነው:: ፓአኔኢ የተባለው በተለያዩ ዘርፎች በልማት-ፓሊሲዎች አወጣጥ ሂደት ላይ ተሳትፎ በማድረግ ድህነትን ለመቀነስ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ የልሆኑ ድርጅቶች አውታር ነው:: ፓአኔኢ በመንግሥት የልማት ፖሊሲዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሚያቀርባቸው አሥተያየቶችና ምክሮች እንዲካተቱ የሚጥረው የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ፣ የፖሊሲ ትንተናዎችን በማካሄድ፣ ግንዛቤ የመስያዝና የአድቮኬሲ ሥራን በመሥራትና መረጃን በማጋራት ነው:: በግልጽ የተቀመጠው የፓአኔኢ ራእይ በኢትዮጵያ ድህነትን ማጥፋትና የሀገሪቱ ዜጐች ክብራቸውና ነፃነታቸው ተጠብቆ ሲኖሩ ማየት ነው:: የፓአኔኢ ተልዕኮው የሰብዓዊ መብት መከበርን እንደመሳሪያ በመጠቀም ዜጐችን አቅም ማላበስ፣ ዜጐች በልማት ፖሊሲዎች አቀራረፅ ፣ ትግበራና የፖሊሲ ክትትልና ግምገማ በሚደረግበት ሥርዓት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማስቻል፣ የድህውን ድምፅ ለውሳኔ ሰጪ አካላት ማቅረብና የሲቪል ማሕበረሰብ አካላትን ማቀራረብ፣ የሲቪል ማሕበረሰብ አካላትን፣ መንግስትንና ለጋሾችን ለደሀው ተጠያቂ ማድረግ ነው::

ፓአኔኢ ድሀውን የሚደግፉ የልማት ፖሊሲዎች ተቀርፀው እንዲወጡ ለማድረግ የአድቮኬሲ ሥራን ከመሥራት ባሻገር የሲቪል ማሕበረሰብ ተቋማትን በመቀስቀስ በፖሊሲ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሲቪል ማህብረሰብ አካል የሆኑ ድርጅቶችንና ከልማት የተገለሉ የአካባቢ ማህበረሰቦችን አይዞህ ባዮቻቸውን ለህልውናቸው ከጀርባቸው ሆነው የሚከራከሩላቸውን ለማጠናከር እንዲሁም እነኝህ አካላት በፖሊሲ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉና እራሳቸው በቀጥታ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ፣ የዜጎችንና በዝቅተኛ እርከን ላይ ያሉ የአካባቢ ድርጅቶች በየደረጃው ካሉ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ጋር ዘላቂ የሆነ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ለመርዳት ይፈልጋል::

ፓአኔኢ በዓይነታቸው ብዙ የሆኑ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን በአባልነት የያዘ ጥምረት ሲሆን እነዚህም የሀገር በቀል የሙያ ማህበራት፣ የምርምር ተኮር ድርጅቶች፣ ሀገር-በቀልና ዓለም-አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የብዙሃን ማህበራት...ወዘተ ሲሆኑ በተጨማሪም በሁሉም ክልል በየደረጃው የሚኖር ተሳትፎን እውን ለማድረግ የሚያስችሉና ዋና አላማቸውም በዝቅተኛ እርከን ላይ ያሉ የአካባቢ ሕብረተሰቦችን እንቅስቃሴ ማስተባበር የሆነ የክልል ቅርንጫፎች አሉት:: የፓአኔኢ የተለያዩ አባል ድርጅቶች በጥምረቱ ሥራ ላይ በቀጥታ የሚሳተፉት እያንዳንዳቸው በድርጅቱ ሦስት ልዩ ትኩረቶች ተመስርተው በተዋቀሩት ዋና ዋና ማዕከላዊ ስብስቦች ውስጥ በአንዱ ውስጥ በመሳተፍ ነው:: ሦስቱ ማዕከላዊ ስብስቦችም:-

- የፖሊሲ ምርምርና ውይይት ማዕከላዊ ስብስብ፣
- የህብረተብ ልማት፣ የትግበራ ክትትልና ግምገማ ማዕከላዊ ስብስብና፣
- የመረጃ፣ የግንኙነትና አድቮኬሲ ማዕከላዊ ስብስብ ናቸው::

የአባል ድርጅቶች ውክልና ያለው የፓአኔኢ ጠቅላላ ጉባኤ የድርጅቱ ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል ሲሆን የሥራ አሥፈፃሚ ቦርዱን የሚመርጠውና የቦርዱንም

እንቅስቃሴ በበላይ የሚቆጣጠረው ይኸው አካል ነው፡፡ የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ በበኩሉ የጥምረቱን ሴክረታሪያት ጠቅላላ እንቅስቃሴ ይከታተላል፡፡ የፓአኔኢ ሴክረታሪያት ደግሞ የጥምረቱን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያከናውን አስፈፃሚ አካል ነው፡፡

ፓአኔኢ ይህንን ጥናት ከላይ እንደተገለፀው በሃገሪቱ ድህ-ተኮር በሆኑ አገልግሎቶች ላይ ዜጎች ያላቸውን አስተያየት በማሰባሰብ አገልግሎቶቹ እንዲሻሻሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው፡፡ ከነዚህ ጥረቶች አንዱ የጥናቱን ውጤቶች በተለያዩ ቋንቋዎች አዘጋጅቶ በየደረጃው ላሉ ልዩ ልዩ አስፈፃሚ የሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በማዳረስ በዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈፃፀምና በክትትልና ግምገማ ሂደት ወቅት ትኩረት እንዲሰጣቸው ማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ተጠቃሎ የቀረበው የጥናቱ ውጤት በሚከተሉት ክፍሎች ተካተው ከላይ የተገለፀውን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ቀርበዋል፡ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች በአራቱ በተመረጡ የአገልግሎት ዓይነቶች (በመጠጥ ውሃ፣ ጤናና የአካባቢ ንፅህና፣ ትምህርት እና በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች) የቀረቡ ሲሆን፣ ዋነኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ተብራርተው ተካተዋል፡፡ በመጨረሻው ክፍሎችም ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ የጥናቱን ግኝቶች መሠረት ያደረጉ የፖሊሲ ጠቋሚዎችና ድምዳሜዎች ተካተው ቀርበዋል፡፡

## 1.3 **የዜጎች አገልግሎት አስተያየት መስጫ ካርድ በኢትዮጵያ**

እ.አ.አ መስከረም 2000 ዓ.ም. የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ተቀባይነት ማግኘታቸው የታሪክ ክስተት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ተያያዥነት ያላቸውንና ተደጋጋፊ የሆኑ የልማት አላማዎችንና የታቀዱ ግቦችን ወደ ዓለም-አቀፍ አጀንዳዎች በማካተት በዓለም-አቀፍ ደረጃ ድህነትን የመዋጋት ጥረት አስፈላጊውን ትኩረትና ቁርጠኝነት እንዲያገኝ አስችሏል፡፡ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈጠረውን ሁኔታ ተከትሎ የየሀገራቱ መሪዎች የምዕተ-ዓመቱን የልማት ግቦች መሳካትን በተመለከተ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ሪፓርት አዘጋጅቶ የማቅረብ ጉዳይ የፖለቲካ መሪዎችን፣ የከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳተፍንና እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ አባላትን፣ ህብረተሰቡን፣ መላውን ህዝብና የመገናኛ ብዙሃንን ማሳተፍ ይጠበቃል፡፡ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በሀገር ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስትና የተባበሩት መንግስታት የሀገር ቡድን በጋራ በመሆን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለመቃኘት የሚያስችል ሥራ ማካሄድ ጀምረዋል፡፡

የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም እና ከዚሁ የቀጠለው ድህነትን ለማስወገድ የፈጣን እድገት /ድማፈዘልዕ/ እቅድ የኢትዮጵያ የዕድገት ገዢ ውጥኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ መርህ ግብሮች /እቅዶች/ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የሚያስችል የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሰፊ አቅጣጫን ከመጠቆማቸው በተጨማሪ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት በድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የቀረፃ፣ የትግበራና የክትትል ሂደት ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ወሳኝ መድረክ ፈጥሮላቸዋል፡፡

የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራምና ድህነትን ለማጥፋት የፈጣን እድገት እቅድ የተለዩ እና ቅድሚያ /ትኩረት/ የተሰጣቸውን ተግባራት በበቂ ሁኔታ ያካተተ የድርጊት እቅድን አስቀምጠዋል:: የአመታዊ አፈፃፀም ደረጃ ሪፖርት ከተቀመጡ የመነሻ መለኪያዎች አንፃር የትግበራ ሂደትን ተቋማዊ በሆነ መልኩ መከታተል ያስችላል:: ምንም እንኳን የዓመታዊ አፈፃፀም ሪፓርት የመነሻ መለኪያዎችን መሠረት ያደረገ የአፈፃፀም ቁርጠኝነት እንዳለ ለመለካት ከአቅርቦት አንፃር የሚታዩ አመላካቾችን ለመመልከት የተነደፈ ቢሆንም የአቅም ተኮር ስልቶችና የማሻሻያ እርምጃዎች የሚያስከትሉትን ለውጥና ያላቸውን የስርጭት ሽፋን ለመፈተሽ የሚያስችል የእይታ አድማስን ለማስፋት እንዲቻል አሳታፊና ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ አመልካቾች አስፈላጊነት እውቅና እያገኘ መጥቷል:: እነዚህ ተመጋጋቢ እርምጃዎች ሰፊ ግንዛቤ እንደሚፈጥሩና የመንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያኖች አስቀድሞ የመሳተፍ ስሜትን እንደሚጭርባቸው ይጠበቃል::

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን መሠረት በማድረግ ወሳኝ የሆኑ የጥራትና የመጠን ስኬቶችን ለመዘርዘር አሳታፊ የሆኑ እንደ ዜአካ ያሉ ዘዴዎች ጥቅም ላይ የዋሉት::

## 1.4 የሙከራ ጥናቱ ንድፍ

ይህ በኢትዮጵያ የተካሄደው የዜአካ የሙከራ ጥናት ፕሮጀክት የሕዝብ ግልጋሎት አሰጣጥ ማሻሻያን በተመለከተ በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉ እጅግ መልካም የሆኑ ተሞክሮዎችን አፈላልጐ ለማግኘት የተደረገ ሙከራ ነው:: የሙከራ ፕሮጀክት እንደመሆኑ መጠን ትኩረት የሠጠው አራት ወሳኝ ዘርፎች ብቻ ነው:: እነዚህም ዘርፎች የመጠጥ ውሃ፣ የጤናና ንፅህና፣ የትምህርትና የግብርና ኤክስቴንሽ አገልግሎቶች ናቸው::

በተመሳሳይ መልኩ የፕሮጀክቱ የስነ ምድር ሽፋኑም አራት የገጠር ክፍሎችን አንዱ የከተማ አካባቢን ብቻ የሸፈነ ነው:: እነዚህም ክፍሎች ትግራይ፣ኦሮሚያ፣ አፋርና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሲሆኑ በጥናቱ የተሸፈነው የከተማ አካባቢ ደግሞ የድሬዳዋ መስተዳደር ነው:: ከአፋር ክልል የተሰበሰበው መረጃ ክፍትና ተለዋዋጭነት የታየበት (ወጥነት የጐደለው) በመሆኑ የጥናቱ ትንተና የአፋር ክልልን አያካትትም:: ነገር ግን በዚህ ክልል ያጋጠመው ችግር ለጥናቱ ሂደት ዋጋ ያለው ትምህርትን ሰጥቶ አልፏል:: ምንም እንኳን ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ቢሆንም ለተለያዩ አጋሮች እውቀትን ከመሥጠቱና አቅማቸውን ከመገንባቱ በተጨማሪ የሕዝብ አገልግሎቶችን ደረጃ ለማሻሻል ፍላጐት ላላቸው አጋሮች የሚጠቅሙና አስተውሎት የተሞላቸው የፖሊሲ ጠቋሚዎችን አመልክቷል::

በፓኔኢ ተነድፎ ተግባራዊ የሆነው ይህ የምርምር ፕሮጀክት ዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ክትትል ሂደት ወሳኝ የሲቪል ማህበረሰብ አካላትን ጠንካራ ድርሻ እንዲኖራቸው ድርጅቱ ሲያደርግ የቆየው ጥረት አካል በመሆን የተጀመረ ነው::

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ወደፊት በተደጋጋሚ ተደርጐ ቀጣይነት ሊኖረው የመቻሉ ጉዳይ የሀገር ውስጥ (ለሀገር በቀል) ተቋማት በሚኖራቸው የአቅም ሁኔታ ይወሰናል:: እንዲህ ያለውን ፕሮጀክት የመንደፍና የዳሰሳ መረጃን የመሰብሰብ ተግባር በብዙ ሀገራት ስራውን የመስራት አቅም ባላቸው ሀገር በቀል በሆኑ

አትራፊ የምርምር ኩባንያዎች ወይንም ደግሞ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች) ይከናወናል። ምንም እንኳን በሀገሪቱ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት አሳታፊ የሆኑ ምርምርን የሚካሄዱ እምቅ አቅም እንዳላቸው አንዳንድ ፍንጮች ቢኖሩም እንደ ዜአካ ዓይነት ጥናቶችን ለማካሄድ የሚያስችል በቂ አቅም ያለው የሀገር በቀል ተቋም እጥረት እንዳለ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ሐቅ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥ ተቋቁመው የሚገኙት ማህበራዊና አትራፊ የሆኑ የምርምር ወኪሎች (ተቋማት) እንደ መልካም እድል ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። የዚህ አባባል እውነትነት የሚጐላው በተለይ ፓአኤኢ የተለያዩ አጋሮቹን ጠንካራ ጐን ተጠቅሞ ስራውን የሚያከናውን የጥምረት ድርጅት በመሆኑ ነው። ነገር ግን ይህ እንዳለ ሆኖ ፓአኤኢ ለግዜው ያለው የሀገር በቀል ተቋማት አቅም የዜአካን ምርምርን ለመንደፍ በቂ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፐብሊክ አፌርስ ፋውንዴሽን (PAF) በመባል የሚታወቀውን የህንድ ሀገር የምርምር ተቋምን በመጋበዝ ስምምነት ላይ በተደረሰበት የአሰልጣኞች ሥልጠና የምርምር ዘዴ ግብዓቶች አማካኝነት የዜአካን ዘዴ በመጠቀም ምርምርን የማድረግ አቅም ተቋሙን እንዲገነባ አድርጓል።

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

የዜአካ የሙከራ ጥናት የቴክኒክ ክፍል የሚከተሉተን ደረጃዎች ያካትታል።

1. በተመሳሳይ የአስተያየት ሰጪዎቸ ውይይት (FGD) አማካኝነት የጥናቱን ጭብጦች መለየት
2. ለጥናቱ የሚሆን መረጃን ለመሠብሠብ የሚያሥችሉ መጠይቆችንና ቅፆችን ማዘጋጀት
3. የናሙና መረጣ ማካሄድ
4. የአሰልጣኖች ስልጠና ማካሄድ
5. መረጃ ሰብሳቢዎችን ለመምረጥና ለማሰልጠን መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣
6. የመስክ ጥናቱን ማካሄድ
7. የመሥክ ሥራ አስቀድሞ በተወሰነ መመሪያ መሠረት መካሄዱን ለመቆጣጠር የሚያስችል የሂደት ቁጥጥር ማከናወን
8. የመረጃ ማቀነባበሪያ ንድፎችን መቅረፅና መረጃን ወደ ኮምፒዩተር የማስገባት ሥራን ማከናውን
9. መረጃን የመተንተንና የመተርጎም ሥራ እንዲሁም
10. ረቂቅ ሪፓርት

## 1.6 የጥናቱን የትኩረት ነጥቦች /ሃሳቦችን/ መለየት

የጥናቱ ዋና ጉዳዮችንና ጭብጦችን ለመለየት በገጠር አካባቢ በተመሣሣይ አስተያየት ሰጪዎች ውይይት ምርመራ ተካሂዷል። ይህ የተመሣሣይ አስተያየት ሰጪዎች ውይይት ምርመራ ዓላማ ወሳኝና ተለዋዋጭነት ያላቸውን የጥናቱን ነጥቦችና ገፅታዎች ለመለየትና ለሙከራ ጥናት የሚሆኑ እትሞችን ለመንደፍ

ነው:: አስቀድመው የተመረጡ ተለዋዋጮች ተዛማጅነት እና ወሳኝነታቸውን ለመለየት /ለመሞከር/ ቋሚ የሆኑ የማውጣጣት ጥያቄዎች ተደርገዋል:: በከፊል ቋሚ እና ለመልስ ክፍት በሆኑ የአውጫጪኝ ጥያቄዎች አማካኝነት ተያያዥነት ያላቸውንና የዘርፉን ልዩ ልዩ ነጥቦችና መረጃዎችን ለመሰብሠብ ተችሏል:: የዳሰሣ መረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎችን ቀረፃ ለማመቻቸት የተመሣሣይ አስተያየት ዘዴንና በቅርብ የሚገኙ ሠነዶችን በማገላበጥ የጥናቱ ዝርዝር ነጥቦች ተለይተዋል:: የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ እና በአማርኛ ተተርጉመዋል::

## ናሙና መለየት ወይም /የናሙና ቤተሰቦችን መለየት/

ኢትዮጵያ በአሥራ አንድ ክልሎች የተከፋፈለች ስትሆን እነዚህ እያንዳንዱ ክልሎች እንደገና በወረዳዎች የተከፋፈሉ ሲሆኑ ወረዳዎቹ ደግሞ በአነስተኛ አስተዳደር ክፍሎች ማለትም ቀበሌዎች የተከፋፈሉ ናቸው:: ይህ ጥናት በአጠቃላይ የአገሪቱ 3900 የሚሆኑ የናሙና ቤተሰቦች ላይ የተመሰረተና የጠቅላላ ሀገሪቱን ሁኔታ የሚወክል ነው:: በጥናቱ በናሙናነት ተመርጠው የተካተቱት የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ከአራቱ የገጠር እና ከአንድ የከተማ ቦታዎች ነው:: ሶስቱ የገጠር ክልሎችም ኦሮሚያ፣ ደቡብና ትግራይ የነበሩ ሲሆን በአጠቃላይ ካለው ያገሪቱ ህዝብ ብዛትና የመሬት ስፋት ውስጥ 85 ከመቶ የሚሆነውን ይሸፍናሉ:: የድሬዳዋ ከተማ የከተሞችን የናሙና ክልል በመወከል ተመርጧል::

**ሰንጠረዥ 1 - የናሙና መጠን በክልል**

| ክልል | የናሙና አመራረጥ አካሄድ | የናሙና መጠን |
|---|---|---|
| **ኦሮሚያ** | ለጥናቱ ከእያንዳንዱ ወረዳ 5 ቀበሌዎች ተመርጠዋል:: በአንድ ወረዳ 300 የሚሆኑ የናሙና ቤተሰቦች በየቀበሌው በሚኖሩ የቤተሠብ ቁጥር መጠን በኩል ድርሻ እንዲኖራቸው በማድረግ ተመርጧል:: ቤተሰቦችን መምረጥ ለሁሉም እኩል ዕድልን የሚሠጠውን የዘፈቀደ የአመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነበር:: ነገር ግን እማወራ ቤተሰቦችን የመምረጥ ሁኔታ ሆን ተብሎ /የተፈልጐ/ የአመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነበር፡ | 1201 |
| **ትግራይ** | ከእያንዳንዱ ወረዳ 9 ቀበሌዎች ተመርጠዋል:: 450 የሚሆኑ የናሙና ቤተሰቦች በየቀበሌው በሚኖሩ የቤተሰብ ቁጥር መጠን እኩል ድርሻ እንዲኖራቸው ተመርጠዋል:: አሥቀድሞ ከተመረጡት እያንዳንዱ ቀበሌዎች ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን የመምረጥ ጉዳይ የዘፈቀደ የአመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነበር:: | 838 |
| **ደቡብ** | ከእያንዳንዱ ወረዳ 7 ቀበሌዎች በዘፈቀደ ከተመረጡ በኋላ 300 ቤተሰቦች በየቀበሌው በሚኖሩ የቤተሰብ ቁጥር መጠን እኩል ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርገው ተመርጠዋል:: ቤተሰቦችን የመምረጥ ጉዳይ የዘፈቀደ የአመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነው፡ | 594 |
| **ድሬዳዋ** | ከአጠቃላይ ዘጠኝ ቀበሌዎች ሁለት ቀበሌዎች በዋነኛነት ተመርጠዋል:: 600 የሚሆኑ የናሙና ቤተሰቦች በሁለቱም ቀበሌዎች እኩል በመክፈል የናሙና ድርሻ እንዲኖራቸው በማድረግ በዘፈቀደ የናሙው የአመራረጥ ዘዴ ተመርጠ ዋል:: | 595 |
| **አጠቃላይ የናሙና ተጠያቂዎች ብዛት** | | 3,228 |

የናሙናው እቅዱ እንደሚያሳየው ከተመረጡት ክልል ውስጥ ከኦሮሚያ በስተቀር ከእያንዳንዱ ክልል ሁለት ሁለቱ ወረዳዎች ተመርጠዋል:: የኦሮሚያ ክልል የህዝብ ብዛቱ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት 4 ወረዳዎች እንዲካተቱ ተደርጓል:: ሁለቱ ወረዳዎች የተመረጡት ለክልሉ ማዕከላዊነት የመቀረብና የመራቅ ሁኔታን በማገናዘብ ሲሆን የአመራረጥ ዘዴውም የእኩል እድል የናሙና ዘይቤን በመከተል ነው:: በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች በቅርበታቸው ወይንም በርቀታቸው ከተደለደሉ በኋላ በናሙናነት የተካተቱት የመጨረሻዎቹ ወረዳዎች ከእያንዳንዱ ሁለቱ ጎራ ከእያንዳንዱ ክልል በዘፈቀደ የአመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል:: ከእያንዳንዱን ክልል ወረዳዎችና ቀበሌዎችን የመምረጥ ሂደት በሰንጠረዥ አንድ ከዚህ በላይ ተጠቅሷል::

## የመሥክ ጥናት ስለማካሄዱ

ጥናቱ የተካሄደው በፓአኔኢ አባላት ሲሆን የተለያዩ የመስክ አባላትን የያዙ ቡድኖች በተለያዩ ክልሎች በማስማራት የመስክ ሥራዎቹ በአንድ ወር ውስጥ ተከናውነዋል።

በመቀጠልም የሥራ ሂደት ቁጥጥር ከአፋር ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች ተካሂዷል። የአፋርን ክልል የመራው አስተባባሪ በመስሪያ ቁሳቁሶች ችግር ምክንያትና ወደ አዲስ አበባ መድረስ ባለመቻሉ ከPAF አማካሪዎች ጋር ባለመነጋገሩ (ባለመገናኘቱ) ምክንያት የሥራ ቁጥጥር ሂደቱን ለመከታተል አልቻለም። ዝርዝር የቁጥጥር ሂደቱን በዚህ ፅሁፍ አባሪ ተደርጓል። ከመስክ ስራ ቁጥጥሩ ሂደት በተጨማሪ በፓኔ አባላት አማካኝነት የመስኩ ስራ /ጥናቱ/ ከመካሄዱ በፊት በተቀጠመጠው መመዘኛ መሠረት ጥናቱ አስፈላጊውን ሂደት የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም በጥናቱ ወቅት የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን በአባላቱ አማካይነት ግልጽ ለማድረግ ተሞክሯል።

## ትንተና

በመጠይቆች አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ ከተተነተነ በኋላ ለእያንዳንዱ ክልል ግምቶች ተገኝተዋል። የየክልሉ ግምት በየራሳቸው የገጠር ቤተሰቦች ቁጥር ድርሻ ክብደት ተሰጥቶት የአገር አቀፍ  የገጠር ግምት ተሰልቷል። የከተማ ግምቶች ለብቻ ቀርበዋል።

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

⇒ ይህ ጥናት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን አስተያየት በዳሰሳ ጥናት ዘዴ ተጠቅሞ በህብረተሰቡ አቅም-ተኮር የሆኑ ግልጋሎቶችን ውጤታማነት ለመከታተል መቻሉን ለመፈተን የተደረገ የመጀመሪያ ደረጃ  ጥናት ነው። በዚህ ምክንያት ይህ የሙከራ ጥናት የደረሰባቸው ግኝቶች ጥቅል አመልካቾች እንጂ ለሁሉም አገልግሎቶች ውክልና ያላቸውና ሁኔታዎችን ሁሉ በትክክል የሚገልፁ አይደለም። በመሆኑም ይህ ሁኔታ የዚህ ጥናት አንደኛው ውስንነት ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል።

⇒ የተጠቃሚዎች በአገልግሎቶች የመርካት ሁኔታ ከአገልግሎቶቹ ከሚጠብቁትና አገልግሎቶቹ ስላላቸው ጥቅም ከሚሰጡት ግምት ጋር በጽኑ ይቆራኛል። በዚህ ረገድ ያሉ ምክንያቶች ከክልል ክልል በእጅጉ ይለያያሉ። ይህ ልዩነት በጥናቱ በጥቅል ተሰልቶ ለተገኘው የእርካታ ደረጃ አንዱን ወይንም የተወሰኑ ክልሎችን በማጉላት ወይንም በማሳነስ ረገድ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። ነገር ግን የጥናቱ ውጤት በጥቅል የተገለፀ በመሆኑ ይህንን አያሳይም። በመሆኑም ይህ ሁኔታ የጥናቱ ሌላኛው ውስንነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

## 2. የጥናቱ ናሙና ቤተሰቦች ማህበራዊና ስነ ህዝባዊ ገጽታ

ለዚህ የዜአካ ጥናት ቁጥራቸው 3,829 የሚሆኑ ቤተሰቦች ከአራት ገጠሮችና ከአንድ የከተማ የኢትዮጵያ ክልል በናሙናነት ተመርጠዋል:: እነዚህ 5 ክልሎች አብዛኛው የኢትዮጵያ ክልል ማለትም (ከ80 በመቶ በላይ የአገሪቱን የህዝብ ብዛት) የያዙ ናቸው:: በትግራይ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በአብዛኛው ከ6-10 የቤተሰብ አባላት ያላቸው እንደሆነ ተገልጿል:: ሌሎች የስነ ህዝባዊ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው::

⇒ በክልሎች መካከል የወንድና የሴቶች ልዩነት ታይቷል:: በኦሮሚያና በድሬደዋ ሴቶች ከወንድ ሲበልጡ በቀሪዎቹ ክልሎች ግን በተቃራኒው ነው ::

⇒ የተመረጡት የናሙና ቤተሰቦችን አባላት የእድሜ ስርጭት ስናየው በጥናቱ እድሜያቸው ከስልሳ ዓመት በላይ የሆኑ በጣም ጥቂት ድርሻ ያሳያል:: በተጨማሪም የሴቶች ድርሻ አነስተኛ ነው::

⇒ ቁጥራቸው አያሌ የሆነ የገጠር ቤተሰቦች የሚኖሩት የሳር ክዳን ባለው ቤት ውስጥ ነው::

### 2.1 የትምህርት አሰጣጥና ትምህርት

⇒ በገጠር ካሉት ህፃናቶች መካከል ወደ 63 ፐርሰንት አካባቢ የሚሆኑት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ:: በዚህ ረገድ ኦሮሚያ 66 ፐርሰንት በመያዝ ቀዳሚ ሲሆን የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች 58 ፐርሰንት በመያዝ ይከተላል:: የትግራይ ክልል 51 ከመቶ ይዟል:: በድሬደዋ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ህፃናት ቁጥር ከፍተኛ ድርሻ (88 ከመቶ) እንደያዘ ተመዝግቧል::

⇒ በሁሉም ክልሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የወንድ ህፃናት ቁጥር ከሴቶቹ ይበልጣል:: በትግራይ ክልል የትምህርት ማቋረጥ ፍጥነት/መጠን ልዩነት በሴቶች ላይ ከፍተኛ ሲሆን በኦሮሚያና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ግን ዝቅተኛ ነው:: በጣም የሚያስገርመው በድሬዳዋ የትምህርት ማቋረጥ ፍጥነት መጠን ከገጠሩ የአገሪቱ አካባቢ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ላይ መገኘቱ ነው::

⇒ በገጠሩ አካባቢዎች ፊዕሞ ትምህርት ተከታትለው የማያውቁ ከጠቅላላው ሲመዘን በአሃዝ ከድሬዳዋ ክልል ከፍ ያሉ ናቸው::

⇒ ድሬዳዋን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች ፊዕሞ ትምህርት ተከታትለው የማያውቁ የአህገሪቱ ህዝቦች የሚገኙት እድሜያቸው ከ60 ዓመታት በላይ ነው:: ይህ የሚያሳየው በቅርብ አመታት ውስጥ መሃይምነትንና የትምህርት ተሳትፎን ለማሻሻል ከፍተኛ ርብርቦሽ መደረጉን ነው::

ከመረጃዎች በመነሳት አጠቃላይ የትምህርት ውጤታማነት ደረጃን ከሥርዓተ ፆታ እና ከክልል አኳያ ስንመለከተው የሚከተሉትን የሚያስገርሙ ነጥቦችን/ መረጃዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡

⇒ በሁሉም ክልሎች ትምህርት ተከታትለው ከማያውቁ የአህገሪቱ ህዝቦች መካከል የሴቶች ድርሻ ከወንዶች ጋር ሲነፃር ከፍተኛ ነው፡፡

⇒ ገጠር ከሚኖሩት የአህገሪቱ ዜጎች ውስጥ ከመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ወደ 3 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው፡፡

⇒ በተቃራኒው በከተማ አካባቢ ወደ አንድ ሶስተኛ የሚጠጉት ግለሰቦች ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ በላይ የተማሩ ናቸው፡፡

## 2.2 የጋብቻ ሁኔታ

⇒ በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍሎች ከሚገኙ ቤተሰቦች ውስጥ ከ60 ፐርሰንት በላይ እድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑት ወንዶችና ሴቶች ያገቡ ናቸው፡፡ በድሬደዋ ክልል ይህ ድርሻ አንድ ሶስተኛ ያነሰ እንደሆነ ታውቋል፡፡ በጣም ከፍተኛ  አሃዝ ያላቸው ሴቶች ፈት እንደሆኑ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ልዩነት የሚያሳየን በንፅፅር በገጠሩ አካባቢ ከፍተኛ ጋብቻ እንዳለ ብቻ ነው፡፡

## 2.3 የሥራ ሁኔታ

⇒ በገጠር የቤተሰቦችን ሥራ ሁኔታ በግልፅ እንደሚያሳየው ሴቶች በአብዛኛው በቤት ውስጥ ተዘውትረው የሚሰሩ ሥራዎችን ሲሰሩ ወንዶች በይበልጥ በግብርናው አካባቢ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡

## 2.4 የመገልገያ አቅርቦት

⇒ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከሚገኙ የአገልግሎት አቅርቦቶች ውስጥ የመንግሥት አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ በናሙናነት ከተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ወደ 83 ከመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አቅርቦት በየቀበሌያቸው ውስጥ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡ የሆነው ሆኖ ይህ ድርሻ /አሃዝ/ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዘቦች ክልል ዝቅ ብሎ 68 ከመቶ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በተቃራኒው የትግራይ ክልል ከፍተኛ ድርሻ ይዞ 99 ከመቶ ሆኖ ይገኛል፡፡

⇒ በሌላ መልኩ የመንግስት የጤና መገልገያ አቅርቦቶች በጣም አናሳ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በጥቅሉ ከአንድ አምሥተኛ በታች የሚሆኑት መላሾች ብቻ የመንግሥት የጤና አቅርቦቶች በቀበሌያቸው ውስጥ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

# 3. ማጠቃለያና የፖሊሲ ጠቋሚዎች

## 3.1 የመጠጥ ውሃ ዘርፍ

⇒ ከዚህ ጥናት የተገኘ አስተያየት እንደሚያሣየው ወደ ሶስት አራተኛ የሚጠጋው በገጠሩ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ለመጠጥና ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚሆን ውሃን የሚቀዳው ከባንቧ ወይም ከጐለበተ ምንጭ ሣይሆን ከኩሬና ከሌሎች የተፈጥሮ ምንጮች ነው።

⇒ የውሃ እጥረትን በተመለከተ ከሁለት የገጠር ተጠያቂዎች ከአንድ በላይ /ሀምሣ ስድስት ከመቶ/ የሚሆኑት ችግሩ እንዳለ ተናግረዋል። በተመሣሣይ መልኩ በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት በከተማ ከሚኖሩ ተጠያቂዎች መካከል አርባ ዘጠኝ ከመቶ የሚሆኑት የውሃ እጥረት ችግር እንደሚገጥማቸው ተናግረዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኩሬ ተጠቃሚዎች ከፍተኛ /94 ከመቶ/ የሆነ የውሃ እጥረት ችግር እንደሚገጥማቸው ሲታወቅ ከእነሱ በመቀጠል 85 ከመቶ የሚሆኑት በአግባቡ ካልተያዘ በእጅ የሚወዘወዝ የውሃ ቧንቧ ተጠቃሚዎች የሆኑ ሰዎች ችግሩ እንደሚገጥማቸው የታወቀ ሲሆን፣ 62 ከመቶ የሚሆኑት በአግባቡ ከተያዘ በእጅ ከሚወዘወዝ የውሃ ቧንቧ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ይኸው የውሃ እጥረት ችግር ይገጥማቸዋል። ክልላዊ የውሃ መረጃ እንደሚያሳየው ወቅታዊ የሆነ የውሃ አጥረት ችግር በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል ከፍተኛ /78 ከመቶ/ ሲሆን፣ ቀጥሎ በኦሮሚያ 51 ከመቶና በትግራይ 40 ከመቶ እንደሆነ ተስተውሏል። በጥናቱ በናሙና ተጠያቂነት ከተካተቱትና የውሃ እጥረት ችግር እንደሚከሠት ከተናገሩት ሰዎች መካከል 54 ከመቶ የሚሆኑት በዚሁ ችግር ምክንያት ውሃን በመደበኛነት ከቧንቧና ከሌሎች በዘመናዊ መንገድ ከጐለበቱ ምንጮች ተጠቃሚነት ወደ ንፅህናቸው ካልተጠበቀ የውሃ ምንጮች እንደተዘዋወሩ ተናግረዋል። በአጠቃላይ ይህ ሁኔታ በሁሉም ክልሎች እንደተከሠተ ለመረዳት ተችሏል።

⇒ ውሃ እንደልብ በሚገኝበት ወቅት (በዝናብ ወቅትና ከእርጥበት ጋር በተያያዘ) ወደ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው ሕዝብ በመኖሪያ ቤቱ 300 ሜትር ክልል ውስጥ ውሃን ያገኛል። ነገር ግን ውሃን በዚህ እርቀት ላይ የማግኘቱ ሁኔታ የውሃ እጥረት በሚከሰትበት ወቅት (በበጋ ወራት) በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሣል። በዚህ ወቅት 11 ከመቶ የሚሆነው የገጠር ነዋሪ ብቻ በመኖሪያ ቤቱ 300 ሜትር ክልል ውስጥ ውሃን እንደሚያገኝ በጥናቱ ተካተው መልስ ከሰጡ ተጠያቂዎች ለመረዳት ተችሏል።

⇒ 44 ከመቶ የሚሆኑት በጥናቱ የተካተቱት ተጠያቂዎች የውሃ ቧንቧዎችን በመጠገን ሥራ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። ይህ ተሣትፎ በአብዛኛው ህብረተሰቡ የጉልበት ሥራን በመስራት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አካል እንደሆነ ተጠቁሟል።

⇒ ከህብረተሰቡ የተገኘ አስተያየት በፅኑ እንደሚያሳየው የወንዞች ውሀ መበከል እየተባባሰ የመጣ ጉዳይ መሆኑ ነው። በጥናቱ ውስጥ በናሙናነት ከተወሰዱት ጠቅላላ የገጠር ነዋሪዎች መካከል ወደ 70 ከመቶ የሚጠጉት የወንዝ ውሃ ተጠቃሚዎች ይኸው የብክለት ችግር እንዳለ ተናግረዋል። ነገር

ግን ይህንን መረጃ ከሰጡት ጥቂቶቹ ብቻ የውሃ ማጥለያ ዘዴን እንደሚጠቀሙ ለመገንዘብ ተችሏል።

⇒ ሳይቋረጥ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ የህዝብ የውሃ ማሰራጫ ቧንቧዎች አስተማማኝ የሆኑ የመጠጥ ውሃ ምንጮች እንደሆኑ ታውቋል። ቀጣይነት ያለው የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ የየክልሉ ሁኔታ ሲታኝ የትግራይ ክልል ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛል። በጥናቱ ለመረዳት እንደሚቻለው 64 ከመቶ የሚሆኑት የትግራይ ክልል የናሙና ጠያቂዎች በክረምት ወራት ለረዥም ጊዜ ውሃን ከቧንቧ ሳይቋረጥ እንደሚያገኙ ተናግረዋል። ነገር ግን የደቡብ ብሄብ ብሄረሰቦችን ናሙና ተጠያቂዎች መልስ ስናይ ሁኔታው በክልሉ የከፋ ሆኖ እናገኘዋለን።

⇒ ተጠቃሚዎች በበቂ ሁኔታ ውሃን እንደልብ የማግኘትና የውሃ ጥራት እርካታን ስንመለከት የህዝብ የውሃ የማሰራጫዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው እናገኛቸዋለን።

⇒ ከውሃ ተጠቃሚ ዜጎች የተገኘው አስተያየት በግልጽ እንደሚያሳየው የውሃ አቅርቦት ጥራት ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ መሻሻልን አሳይቷል። ይህም የመሻሻል ሁኔታ በአብዛኛው የታየው በህዝብ የውሃ ማሰራጫ አገልግሎቶች ላይ ነው።

⇒ አብዛኞቹ በጥናቱ የተካተቱ የናሙና ተጠያቂዎች እንዳመለከቱት የውሃ አገልግሎት ሁኔታ ቢሻሻል ተጨማሪ የውሃ ክፍያ ለመክፈል ዝግጁ ናቸው።

⇒ የውሃ አገልግሎት ሁኔታን ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብለው የተሰጡ አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት የህዝብ የውሃ አቅርቦት አውታሮችን በማስፋፋት ለተጨማሪ ተጠቃሚዎች ውሃን ማዳረስ አስፈላጊ ነው።

## የፖሊሲ ጠቋሚዎች

⇒ ምንም እንኳን በመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ወቅት የንፁህ መጠጥ ውሃን ለማዳረስ በተግባር ላይ የዋሉ ሥራዎች ከፍተኛ መሻሻልን ቢያመጡም፣ ከንፁህ ውሃ አቅርቦት ተጠቃሚ የመሆን ጉዳይ ለብዙ ኢትዮጵያውያን አንገብጋቢ ችግር ሆኖ ቀጥሏል።

⇒ የህዝብ የውሃ አገልግሎት ማሠራጫ አውታርን ከማስፋፋት ባሻገር የተፈጥሮ የውሃ ምንጮችን /ወንዝ፣ ንጽህናቸው ያልተጠበቀ ምንጮችና ኩሬዎች/ አስተማማኝነት ማሻሻል ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ ነው። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ የውሃ እጥረት በሚከሰትበት በበጋ ወራት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከእነዚህ የውሃ ምንጮች ስለሚጠቀም ነው።

⇒ በተለያዩ ቦታ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የውሃ እጥረት በሚከሰትበት በበጋ ወቅት በማንኛውም የጥራት ደረጃ ላይ ያለ ውሃን ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ያጋጥማቸዋል። በመሆኑም በእቅድ የተያዙ መርሃ ግብሮችንና ሌሎች ጠቃሚ ዘዴዎችን በፍጥነት ነድፎ ሥራ ላይ በማዋል ህብረተሰቡን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ችግሩን እንዲቋቋም መርዳት ያስፈልጋል።

⇒ የአዳዲስ የውሃ ሀብት ምንጮች ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ እንደ የውሃ ማቆር ዘዴን የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎች ተለይተው መታወቅ እና ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው::

⇒ እንደ ውሃ፣ መብራትና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች አጠቃቀም በተመለከተ ህብረተሰቡን ሊያሳትፉ የሚችሉ መድረኮችን በመፍጠር የህብረተሰቡን ተሳትፎ እውን ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም እንደነዚህ ያሉ የተሳትፎ መድረኮችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ከውሃ ጋር በተያያዘ የቅስቀሳ መርሃ ግብሮችን ማካሄድ ይቻላል::

⇒ ክፍት ስለሆኑ የውሃ ምንጮች የብክለት መጠንና ውሃን ለማጥለል የሚያስችሉ ዘዴዎችን የመጠቀም ሁኔታ ዝቅተኛነት የተሰጠውን አስተያየት በመገንዘብና ችግሩ አስከፊ እንደሆነ በመረዳት የውሃ ማጥለያ መሣሪያዎች ተገዝተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጎማ ለማድረግ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ መኖር አለበት::

⇒ የዳሰሳ ጥናቱ ውሃን ማግኘት በመቻልና የአስተማማኝ የውሃ አቅርቦት በመኖር ረገድ በክልሎች መካከል የሰፋ ልዩነት እንዳለ ግልፅ አድርጓል:: ይህንን ልዩነት ለማጥበብ የማስተካከያ እርምጃዎችን ነድፎ በፍጥነት ችግሩን መፍታት ያስፈልጋል::

⇒ ለተሻለ የውሃ አገልግሎት ተጨማሪ ክፍያ ለመክፈል ሙሉ ፍቃደኝነት እንዳለ በጥናቱ በናሙናነት በተካተቱ አብዛኞቹ ተጠያቂዎች የተሰጠው አስተያየት በጥንቃቄ መተንተን አለበት:: በዚህ ረገድ ያለው አንዱ አማራጭ በመንደር ወይንም በቀበሌ ደረጃ አነስተኛ የሆነ የውሃ ማሻሻያ ቧንቧዎች ሥራ ነድፎ በመንግስት ድጎማ የታገዘ አነስተኛ የሆነ መዋጮ ከተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲደረግ ማድረግ ነው::

## 3.2 ጤናና የንፅህና አገልግሎት

⇒ የወባ በሽታ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ዋነኛ በሽታ እንደሆነ በጥናቱ በተካተቱ አስተያየት ሰጭዎች በተደጋጋሚ ተጠቅሷል:: ከወባ በመቀጠል ሳል እና ጉንፋን በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል::

⇒ የመንግስት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚጣበቡት በአብዛኛው ፈውስን በሚሹ በሽተኞች ነው:: ይህ ሁኔታ በትግራይ ክልል የጐላ ሆኖ ሲታይ በኦሮሚያና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የግል ሕክምና መስጫ ተቋማት በአንፃራዊ በበለጠ ሁኔታ ሕብረተሰቡ ይጠቀምባቸዋል:: ተገልጋዮች በመንግሥት ተቋማት ለመገልገል ከማይፈልጉበት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ የመድሃኒት አለመገኘት፣ የተቋማቱ እርቀትና ጥራቱ የወረደ አገልግሎት መስጠት ናቸው::

⇒ ለአብዛኛው የገጠሩ ሕብረተሰብ የጤና አገልግሎት በአቅራቢያው አለመኖር ከፍተኛ ችግር ነው:: ችግሩ በትግራይ ክልል እጅግ የከፋ ነው:: በዚሁ ክልል 45.5 ከመቶ የሚሆነው በሽተኛ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ከ10 ኪ.ሜ በላይ መጓዝ ግድ ይለዋል:: ወደ ሁለት ሰስተኛ የሚሆኑት

በሽተኞች ወደ ጤና አገልግሎት ተቋማት ለመድረስ በእግራቸው መጓዝ አለባቸው::

⇒ በመንግሥት የጤና ተቋማት የፈውስ ሕክምና ማግኘት ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል:: የመድሃኒቱ ዋጋን በተመለከተ በክልሎች መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ይስተዋላል::

⇒ ምንም እንኳን በጤና አገልግሎት ተቋማት የዶክተሮች መገኘት ሁኔታ አነስተኛ ቢሆንም ፓራሜዲኮች ግን በአብዛኛው ይገኛሉ::

⇒ ከመንግሥት የጤና አገልግሎት ተቋማት መድሀኒት በነፃ የሚወስዱ ሰዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው:: ይህ ሁኔታ ምናልባትም በተግባር ላይ እየዋለ ካለው የጤና ፖሊሲ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው::

⇒ በሕፃናት ክትባት የቁጥር መብዛት ፍጥነት ረገድ የተሠጠው በከፍተኛ ደረጃ የሚያበረታታ አስተያየት ለመንግሥት የጤና አገልግሎት ሥርዓት በእርግጠኝነት አበረታች ነው:: ነገር ግን በድሬዳዋ ከተማ በዚህ ረገድ የተሠጠው ዝቅተኛ የሆነና የማያበረታታ አስተያየት ሊታሰብበት ይገባል:: በፆታ መካከል ያለው የክትባት ልዩነትም ሊጤን ይገባዋል::

⇒ ከየሁለት ተጠያቂዎች አንዱ/ዷ አጠቃላይ የሆነ የመረጃና ምክር አገልግሎት ከጤና ተቋማት እንደሚያገኙ ቢናገሩም በጣም ጥቂት የሆኑት ተጠያቂዎች ብቻ ስለ ወሊድ መከላከያ ጤና ከነዚህ ተቋማት መረጃ እንደሚያገኙ ተናግረዋል::

⇒ ወደ 50 ከመቶ የሚሆኑት ተጠያቂዎች በጤና ግልጋሎት ረገድ ሙሉ በሙሉ እንደሚረኩ ገልፀዋል: ይህ ሁኔታ በተለያዩ የጤና ግልጋሎት አመላካቾች ሲታይ ከፍተኛው የተገልጋዮች እርካታ የተገኘው እንደተገልጋዩ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ከሚጠብቀው የወረፋ ጊዜና ከሠራተኞች ሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ነው::

⇒ በገጠር አካባቢ ከሚኖሩት ተጠያቂዎች 64 ከመቶ የሚሆኑት ባለፉት 2 አመታት በጤና ግልጋሎት አሰጣጥ ሁኔታ መሻሻል ታይቷል ማለታቸው የሚያበረታታ ነው:: ትልቁ መሻሻል እንዳለ የተገለፀው በኦሮሚያ ክልል ነው::

⇒ ከአንድ ሦስተኛ በታች የሚሆነው በገጠር የሚኖረው ተጠያቂ ለመፀዳጃ ሽንት ቤትን እንደሚጠቀም ተናግሯል:: ሽንት ቤት ያለመጠቀም ባህል ሽንት ቤት መጠቀም ላለመቻል እንደዋና ምክንያት ተደርጎ ተጠቅሷል:: ከሶስት አራተኛ በላይ የሆኑት ሽንት ቤትን የማይጠቀሙ ተጠያቂዎች የሰጡት ምክንያትም ይህንኑ ነው::

⇒ የህዝብ ሽንት ቤት ተጠቃሚ ከሆኑት ተጠያቂዎች መካከል ከግማሽ የሚያንሱት በሽንት ቤት ግልጋሎት ሙሉ በሙሉ ደስተኞች ናቸው:: የሽንት ቤት ማፍሰስ፣ መንጣለል ወይም መጥፎ ሽታ /በተለይ በኦሮሚያ/

በሕዝብ ሸንት ቤት አገልግሎት ላለመርካት እንደ ዋነኛ ምክንያቶች ተደርገው ተገልፀዋል፡፡

⇒ በአጠቃላይ ከገጠር አካባቢ የተገኘው አስተያየት እንደሚያሣየው ባለፉት ሁለት አመታት የንፅህና አገልግሎት እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

## የፖሊሲ ጠቋሚዎች

⇒ የጤና አገልግሎት ተቋማት ከመኖሪያ ቦታ ርቀው መገኘታቸው ትልቅ አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ የጤና ማዕከሎችንና የመጀመሪያ ጤና ክሊኒኮችን በመላ ሀገሪቷ መክፈት ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡

⇒ ስለ መድሃኒት ዋጋ ሰፊ ልዩነት መኖር የተሰጠው አስተያየት የመድሃኒት ፖሊሲን እንደገና መመርመር እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡

⇒ በአስተማማኝ የንፅህና ተግባርና ረገድ የግንዛቤ ማዳበሪያ ዘመቻዎችን ማድረግና ያለውን ሥርዓት ማሻሻል ግልፅ የሆኑና አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 3.3 ትምህርት

- የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ አብዛኞቹ ተማሪዎች ይማሩባቸዋል፡፡

- አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርት ቤቶቻቸውን በመኖሪያ ቤቶቻቸው አካባቢ በ3 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ያገኟቸዋል፡፡ ነገር ግን በትግራይ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት ተማሪዎች ትምህርት አገልግሎትን ለማግኘት ከ5 ኪ.ሜ በላይ ይጓዛሉ፡፡

- ጥናቱ በትምህርት ቤቶች ከፍተኛ የሆነ የውሃ ችግር እንዳለ ጠቁሟል፡፡ በዚህም መሠረት በሚማሩበት ትምህርት ቤት አገልግሎት እንዳለ የተናገሩት ከአጠቃላይ በጥናቱ ከተካተቱት የገጠር ተማሪዎች ከአንድ ሶስተኛ የሚያንስ ቁጥር ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

- በጥናቱ መምህራን ምቹ በሆነ መልኩ ከሥራ ገበታቸው ላይ የመገኘታቸው ሁኔታ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

- የትምህርት አገልግሎትን ለማግኘት የሚያስፈልገው ወጪ ከክፍል ክፍል ይለያያል፡፡ ይህ ግኝት ምናልባትም በሥራ ላይ እየዋለ ያለውን የትምህርት ፖሊሲ መፈተሽ እንደሚያስፈልግ ነው፡፡ ከአንድ ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት ቤተሰቦች ለተለያዩ የትምህርት ቤት አስተዳደሮች ተጨማሪ ክፍያ እንደሚከፍሉ የገለፁ ሲሆን ከነዚሁ ውስጥ 17 በመቶ የሚሆኑት ይህን ተጨማሪ ወጪ ሊያወጡ የቻሉት ግድ ሆኖባቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

- ትምህርት ቤቶችን በማስተዳደር ረገድ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ተሳትፎ መደበኛ ያልሆነና በዘፈቀደ የሚደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡ ምንም እንኳን ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው በጥናቱ

በናሙናነት የተሣተፉ ቤተሰቦች የቤተሰብና መምህራን ጥምር ኮሚቴዎች መዋቀራቸውን እንደሚያውቁ ቢናገሩም እጅግ ጥቂት የሆኑት ቤተሰቦች ብቻ በኮሚቴው ውስጥ አባል እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

- የተማሪ ቤተሰቦች በትምህርት ጥራትና በመምህራን ሥነ-ምግባር ረገድ ከፍተኛ እርካታ እንዳላቸው ቢገልፁም የትምህርት ቤት ህንፃንና ሽንት ቤቶችን በተመለከተ በአንፃራዊ ዝቅተኛ የሆነ እርካታ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

## የፓሊሲ ጠቋሚዎች

⇒ የዳሰሣ ጥናቱ በትምህርት ጥራት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት በክልሎች መካከል እንዳለ ያሣያል:

⇒ የንፁሕና አሥተማማኝ የውሃ መጠን አቅርቦትን በተመለከተ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ወሣኝ የሆነ የውሃ የመሠረት ልማት አውታር በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል እንዳለበት ነው፡፡

⇒ በተጨማሪም ለመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚከፈለው የወርሃዊ ክፍያ መጠን በትምህርት ቤቶች መካከል ሠፊ ልዩነት የሚታይበት መሆኑ በሥራ ላይ የዋሉ ፓሊሲዎችን እንደገና መመርመርንና በግል ትምህርት ቤቶች ደረጃና ሥነ-ምግባር ላይ ውሳኔ መሥጠትን ይጠይቃል፡፡

⇒ የቤተሰብና መምህራን ጥምር ኮሚቴዎች ውስጥ የታየው የአባልነት ቁጥር ዝቅተኛ የመሆኑ ምክንያት ተጠንቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በሌላ መልኩም ከቤተሰብ መምህር ኮሚቴ በተጨማሪ ሌላ የሕተብረሰቡን ተሣትፎ በበለጠ የሚያሳድግ አማራጭ ካለና ውጤታማ ሆኖ ከተገኘ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

## 3.4 የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች

⇒ ከተለያዩ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች መካከል የሰብል ማምረትና የከብት እርባታ በይበልጥ ተስፋፍተው የሚገኙ ሆነው ተመዝግበዋል፡፡

⇒ አርሶ-አደሮች ከግብርና ኤክስቴንሽን በአብዛኛው የሚያገኙት እርዳታ በሰብል ማምረት ዘዴዎች ላይ ሲሆን የመንግሥት የኤክስቴንሽን ወኪሎች አብዛኞቹ አርሶ-አደሮች ለመረጃ ቅርበት እንዲኖራቸውና አዳዲስ ክሕሎቶችን እንዲያዳብሩ በማድረግ በኩል ከፍኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

⇒ የግብርናውን ምርት ግብይት እና የግብአቶች አቅርቦትን በተመለከተ የሚሰጡ ድጋፎች በጣም ደካማ እንደሆኑ ተነግሯል፡፡

⇒ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን ወኪሎች አቅርቦት በየቀበሌያቸው ውስጥ /አካባቢ/ እንዳሉ ቢገልፁም ከሞላ ጎደል ለአገልግሎቱ ቅርበት ያላቸው ሆነው የሚገኙት አነስተኛ ድርሻ /ቁጥር/ ያላቸው ናቸው፡፡

⇒ ከእጅ ወደ አፍ ተፈጥሮ ላይ የተወሰነ ኢኮኖሚ ባለበት 26 በመቶ የሚሆኑት ገበሬዎች ስለ ግብርና እና መሰል ሥራዎች /እንቅስቃሴዎች/

ብድር ማግኘታቸውን ገልጸዋል። የብድር ምንጮቹም በየክልሉ ይለያያሉ። በጣም ጥቂት ገበሬዎች ብቻ ብድር ለማግኘት ወደ መንግስት ተቋማት ሄደዋል። ነገር ግን ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ያለምንም ከባድ ችግር ብድር ማግኘታቸውን ገልፀዋል።

⇒ ግብይት የተለመደ ሲሆን መደበኛ የሆነ የገበያ ድጋፍ ጨርሶ የሌለ ይመስላል። 37.5 ከመቶ የሚሆኑት ተጠያቂዎች ናቸው ለምርቶቻቸው ትክክለኛ ዋጋ እንደሚያገኙ የተናገሩት። ነገር ግን ስለወቅቱ የገበያ ሁኔታ ያለው እውቀት ከፍተኛ ነው።

⇒ ከገጠር ቤተሰቦች ውስጥ ወደ 10 በመቶ የሚሆኑት በምግብ እጥረት ምክንያት ተገደው ይሰደዳሉ ። ይህም ድርሻ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በጣም ከፍ ያለ ነው /15 ከመቶ/

⇒ ከግማሽ በመቶ በላይ የሚሆኑ ገበሬዎች የሰብል መበላሸት እና የከብቶች እልቂት እንደሚያጋጥማቸው ገልፀዋል።

⇒ በኤክስቴንሽን ሠራተኞች ስለሚሠጠው አገልግሎት የተሠነዘረው አስተያየት እንደሚያሳየው የሚሠጡት አገልግሎቶች ጠቃሚ፣ ጊዜን የጠበቁና፣ አስፈላጊ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ አገልግሎቶች በቂ ናቸው ያሉት ከጠቅላላዎቹ ተጠያቂዎች 56 ከመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው።

⇒ ምንም እንኳን በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ረገድ ያለው የእርካታ ደረጃ ዝቅተኛ ቢሆንም የገጠሩ ተጠያቂ አገልግሎቱ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ መሻሻል እንዳሳየ አስተያየቱን ሰጥቷል።

⇒ አገልግሎትን ለማሻሻል መወሰድ ስላለበት እርምጃ ገበሬዎች አስተያየታቸውን እንዲሠጡ ተጠይቀው የሰጧቸው አስተያየቶች በአብዛኛው የሚያገናኙት የዘመናዊ ማዳበሪያ ዋጋን ከማሻሻል ጋር ነው።

## የፓሊሲ ጠቋሚዎች

⇒ የግብርናና ከግብርና ጋር የሚያያዙ ሥራዎች ለገጠር ኑሮ መሻሻል ወሳኝ በመሆናቸው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህ የዳሰሳ ጥናት የኤክስቴንሽን ሠራተኞች የቴክኒክ እውቀትን ለገበሬዎች በማሥጨበጥና እንዲዋሀዳቸው በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወቱ ያስረዳል። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያለውን የኤክስቴንሽን ሠራተኞች አውታርን ማስፋፋት ስለማስፈለጉ ጠንካራ የሆነ አስተየያት እንዳለ ጥናቱ ያሳያል።

⇒ የግብርና ምርቶች ገበያ እንዲያገኙና ገበሬው የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ድጋፍ ማድረግ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም ገበሬዎች ለምርቶቻቸው ጥሩ ያልሆነ ዋጋ የሚያገኙ ይመስላቸዋል። ይህ ጉዳይም ሊመረመር ይገባዋል።

⇒ ከፍተኛ እጅ የሚሆኑት ገበሬዎች በየጊዜው እህሎቻቸውንና ከብቶቻቸውን በድርቅና በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚያጡ ተናግረዋል። ይህም የሚጠቁመው የዋሥትና ሥርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ነው።

## 4. ዘርፎችና ክልሎች እንዴት ይለካሉ?

ይህ የዜአካ የሙከራ ጥናት በአራት ክልሎች (በሦስት የገጠርና በአንድ የከተማ ክልል) በሚገኙ አራት ድሃ ተኮር ግልጋሎቶች መጠነ ሰፊ የሆኑና ትኩረትን የሚስቡ ግኝቶችን አመላክተዋል። በዚህ ንዑስ ክፍል በግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን ሂደት፣ አጠቃቀም፣ የግልጋሎቶች ጥራት ወይም አስተማማኝነት እና በግልጋሎቶች በተመለከተ ተጠቃሚዎች ያላቸው ጥቅል የእርካታ ደረጃ ሁኔታዎችን በተመረጡ በቁጥር በሚለኩና በቁጥር በማይለኩ መመዘኛዎች በመጠቀም አራቱን ግልጋሎቶች ለማወዳደር ተሞክሯል።

### I. የግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን እድል ማግኘት

ወሳኝ የሆነ የሕዝብ መሠረተ ልማት አውታር መኖርና የግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን ሁኔታ የሕዝብ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ለመለካት ጥሩ አመልካች ሊሆን ይችላል። በዚህ ጥናት እያንዳንዱ አራቱ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን ሁኔታን /እድልን/ የሚያሳዩና የተመረጡ መለኪያዎች የሚከተሉት ናቸው

⇒ **የጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ:-** የህክምና ግልጋሎትን ከመኖሪያ ቤታቸው በሦስት ኪ.ሜ ክልል ውስጥ እንደሚያገኙ የገለፁ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

⇒ **የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ:-** በቀበሌ ገበሬ ማህበራት ውስጥ ትምህርት ቤት አለ ብለው የተናገሩ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

⇒ **የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት:-** ለቀበሌአችን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተወካይ /ሠራተኛ ተመድቧል ብለው የተናገሩ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

### II. ከሕዝብ የአገልግሎት ተቋማት ግልጋሎትን የመጠቀም ሁኔታ

የተለያዩ የሕዝብ ግልጋሎቶችን የመጠቀምን ሁኔታን ከሚያሳይ መግለጫ መረዳት እንደሚቻለው ዜጎች ምን ያህል በነዚህ ግልጋሎቶች ላይ የተመሰረቱ እንደሆነ ለመረዳት ከማስቻሉም በላይ ከሕዝብ አገልግሎቶች በተጨማሪ ያሉ ሌሎች አማራጭ አገልግሎቶች ስለመኖራቸው መረጃ ለማግኘት ያስችላል። የሚከተሉት ከአገልግሎት የመጠቀምን ሁኔታ የሚያሳዩ የተጠቃሚነት መለኪያዎች በዚህ ጥናት ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል። የየአገልግሎቶቹ መለኪያዎች ከዚህ በታች የተገለፁት ናቸው።

⇒ **የመጠጥ ውሃ:-** የሕዝብ የውሃ ተቋማት (ከቦኖዎች ከእጅ ፓምፖች እና ከቤት ውስጥ ቧንቧዎች) ተጠቃሚዎች ብዛት ከመቶ

⇒ **የጤና አገልግሎቶች :-** ከሕዝብ የጤና ተቋማት ተጠቃሚዎች ብዛት ከመቶ

⇒ ***የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት:-*** *የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተጠቃሚዎች ብዛት ከመቶ*

⇒ **የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች:-** በግብርና *መምሪያ* የሚሠጡ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች ቁጥር ብዛት ከጠቅላላ የቤተሰብ ቁጥር ያለው ድርሻ

## III. የሕዝብ ግልጋሎቶች ጥራት/ አስተማማኝነት

የሕዝብ ግልጋሎቶች ጥራት /አስተማማኝነት/ ደረጃን ለማወቅ በሚፈለግበት ጊዜ በአግባቡ የተቀመጡ የተለያዩ የቴክኒክ መለኪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ:: ለምሳሌ የከርሰ ምድር የውሃ ምንጮች በካሎሪ የመበከል መጠንን ለመለካት እንደሚያስችለው እንደ የናይትሬት ማረጋገጫ ሙከራ ወይንም የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን ዝንባሌ ለመለካት እንደሚረዳው የእውቀት ቀሳሚዎች የውጤት (ስኬት) ማረጋገጫ ሙከራ ዘዴዎች ናቸው::

እነዚህ ዘዴዎች የአንድን አገልግሎት ጥራት /አስተማማኝነት/ የሚለኩት ከአገልግሎቶቹ አንፃር እንጂ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑት ሰዎች አንፃር አይደለም:: የዚህ አይነት የአመዛዘን ዘዴን መጠቀም በስፋት የተለመደ ነው:: ነገር ግን የአንድን አገልግሎት ከተጠቃሚዎች አንፃር በምናይበት ጊዜ እውነታው የተለየ ነው:: ለምሳሌ ያህል ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ብዙ ተጠቃሚዎች አንድ ግልጋሎት ሳይቋረጥ ለረጅም ጊዜ የመቆየት ሁኔታ ቁልፍ የሆነ የግልጋሎት ጥራትን የሚለኩበት መመዘኛቸው ነው:: የዚህን ጥናት ትንተና ለማካሄድ ሲባል የሚከተሉት የጥራት /አስተማማኝነት/ ገፅታዎች ከተጠቃሚዎች አንፃር ታይተው እንደ መመዘኛ አመለካቾች ተደርገው ተወስደዋል::

⇒ **የመጠጥ ውሃ:-** ለረጅም ጊዜ ሣይቋረጥ የሚቆይና በቂ (እንደልብ) የሆነ የውሃ አገልግሎት እናገኛለን ብለው የተናገሩ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

⇒ **የጤና አገልግሎት:-** ከመንግሥት የጤና ተቋማት መድሃኒት ወስደን ከተጠቀምን በኋላ ፈውስ እናገኛለን ብለው የተናገሩ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

⇒ **የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች :-** በኤክስቴንሽን ወኪሎች አማካኝነት የሚሠጠው አገልግሎት በቂ፣ ወቅትን የጠበቀ፣ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ብለው የተናገሩ ተጠያቂዎች ቁጥር ከጠቅላላ ተጠያቂዎች ቁጥር ብዛት ያለው ድርሻ

## IV. በመንግሥት አገልግሎቶች የመርካት ሁኔታ

እርካታ የሚለው ቃል የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለ አገልግሎት አፈፃፀም ያላቸውን ግምገማ ይወክላል፡፡ ምንም እንኳን ይህ ጥናት (ለግልጋሎቶች ጥራት ትኩረት ለመሥጠት ሆን ተብሎ በተቀየሰ ሥልት ምክንያት) ተጠያቂዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሰጡትን ጠቅላላ የእርካታ መጠን ውጤት ድምር ያቀረበ ቢሆንም ለትንተና ጥቅም ላይ የዋሉት ውጤቶች ሙሉ በሙሉ በአገልግሎት መርካትን የሚያመላክቱት ናቸው፡፡

ለማጠቃለያ የደረጃ ምደባ ሲባል ለእያንዳንዱ ግልጋሎት አብላጫ ክብደት ተሰጥቶ የተመዘገቡ ድምር ውጤቶች ተበጅተዋል፡፡

⇒ የዘርፎች የደረጃ ምደባ እንደሚያሳየው የትምህርት ዘርፍ መሪነትን ሲይዝ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሁለተኛ ደረጃን እንዲሁም የጤና አገልግሎት ሦስተኛ ደረጃና የመጠጥ ውሃ አገልግሎት አራተኛ ደረጃን ይይዛሉ፡፡

⇒ የክልል የደረጃ ምደባ እንደሚያሳየው የትግራይ ክልል የአንደኛ ደረጃነትን ሲይዝ፣የኦሮሚያ በሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

## አባሪ ፡ ሰንጠረዥ2-9

**ሰንጠረዥ 2፡ በመጠጥ ውሃ አቅርቦት መጠን ላይ የዜጎች የእርካታ ደረጃ ከውሃው ምንጭ ጋር ሲነፃፀር**

*( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)*

| ውሃ ምንጭ | የእርካታ ደረጃ | ትግራይ | ኦሮሚያ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ገጠር ድምር | ድሬዳዋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንዝ | ሙሉ በሙሉ | 49.3 | 54.4 | 36.8 | **45.9** | |
| | በከፊል | 9.7 | 34.9 | 31.6 | **30.0** | |
| | አልረካሁም | 41.1 | 13.8 | 31.6 | **24.1** | |
| የጎለበቱ ምንጮች | ሙሉ በሙሉ | 33.3 | 54.1 | 31.8 | **51.9** | |
| | በከፊል | 33.3 | 22.1 | 40.9 | **23.8** | |
| | አልረካሁም | 33.3 | 23.8 | 27.3 | **24.3** | |
| ያልጎለበቱ ምንጮች | ሙሉ በሙሉ | 59.7 | 50.6 | 41.7 | **51.4** | |
| | በከፊል | 10.6 | 16.7 | 33.3 | **16.5** | |
| | አልረካሁም | 29.6 | 32.7 | 25.0 | **32.1** | |
| ኩሬዎች | ሙሉ በሙሉ | 0.0 | 16.1 | 6.9 | **10.5** | |
| | በከፊል | 33.3 | 16.1 | 73.0 | **50.0** | |
| | አልረካሁም | 66.7 | 67.7 | 20.1 | **39.5** | |
| የእጅ ቧንቧዎች (የተሸፈኑ) | ሙሉ በሙሉ | 33.3 | 50.0 | 0.0 | **37.0** | |
| | በከፊል | 0.0 | 5.0 | 45.5 | **15.2** | |
| | አልረካሁም | 66.7 | 45.0 | 54.5 | **47.8** | |
| የእጅ ቧንቧዎች (ያልተሸፈኑ) | ሙሉ በሙሉ | 100.0 | 42.9 | 5.5 | **11.6** | |
| | በከፊል | 0.0 | 0.0 | 52.1 | **44.2** | |
| | አልረካሁም | 0.0 | 57.1 | 42.5 | **44.2** | |
| የህዝብ ቦኖዎች | ሙሉ በሙሉ | 88.0 | 73.3 | 21.7 | **59.3** | 58.2 |
| | በከፊል | 9.0 | 16.0 | 71.0 | **31.9** | 30.6 |
| | አልረካሁም | 3.0 | 10.7 | 7.2 | **8.8** | 11.2 |
| የህዝብ የእጅ ቧንቧዎች | ሙሉ በሙሉ | 64.3 | 40.0 | 13.8 | **50.0** | |
| | በከፊል | 8.0 | 60.0 | 62.1 | **25.4** | |
| | አልረካሁም | 27.6 | 0.0 | 24.1 | **24.6** | |
| ቦርሆሎች | ሙሉ በሙሉ | 64.3 | | | | |
| | በከፊል | 8.0 | | | | |
| | አልረካሁም | 27.6 | | | | |
| ከውሃ ሻጭ ነጋዴዎች የተገዛ | ሙሉ በሙሉ | | 100.0 | | **66.7** | 42.2 |
| | በከፊል | | | 100.0 | **33.3** | 30.2 |
| | አልረካሁም | | | | **0.0** | 27.6 |
| የቤት ውስጥ ቧንቧዎች | ሙሉ በሙሉ | | 100.0 | 33.3 | **60.0** | 79.7 |
| | በከፊል | | | 33.3 | **20.0** | 14.2 |
| | አልረካሁም | | | 33.3 | **20.0** | 6.1 |

**ሰንጠረዥ 3፡ በመጠጥ ውሃ ጥራት ላይ የዜጎች የእርካታ ደረጃ ከውሃው ምንጭ ጋር ሲነፃፀር**

*( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)*

| የውሃ ምንጭ | የእርካታ ደረጃ | ትግራይ | ኦሮሚያ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ገጠር ጠቅላላ (ድምር) | ድሬዳዋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንዝ | ሙሉ በሙሉ | 14.0 | 26.9 | 17.2 | **21.4** | |
| | በከፊል | 10.6 | 4.8 | 3.7 | **5.4** | |
| | አልረካሁም | 75.4 | 68.3 | 79.1 | **73.2** | |
| የጎለበቱ ምንጮች | ሙሉ በሙሉ | 90.0 | 60.3 | 54.5 | **60.1** | |
| | በከፊል | | 6.6 | 9.1 | **6.9** | |
| | አልረካሁም | 10.0 | 33.1 | 36.4 | **33.0** | |
| ያልጎለበቱ ምንጮች | ሙሉ በሙሉ | 27.8 | 24.4 | 16.7 | **24.4** | |
| | በከፊል | 7.9 | 4.5 | 16.7 | **5.3** | |
| | አልረካሁም | 64.4 | 71.1 | 66.7 | **70.3** | |
| ኩሬዎች | ሙሉ በሙሉ | | 16.9 | 1.3 | **7.6** | |
| | በከፊል | 33.3 | 5.1 | 0.6 | **2.3** | |
| | አልረካሁም | 66.7 | 78.0 | 98.1 | **90.1** | |
| የእጅ ቧንቧዎች (የተሸፈኑ) | ሙሉ በሙሉ | 33.3 | 95.0 | 18.2 | **76.1** | |
| | በከፊል | | 0.0 | 9.1 | **2.2** | |
| | አልረካሁም | 66.7 | 5.0 | 72.7 | **21.7** | |
| የእጅ ቧንቧዎች (ያልተሸፈኑ) | ሙሉ በሙሉ | 66.7 | 16.7 | 1.4 | **3.6** | |
| | በከፊል | 33.3 | 16.7 | 4.1 | **6.0** | |
| | አልረካሁም | | 66.7 | 94.5 | **90.5** | |
| የህዝብ ቦኖዎች | ሙሉ በሙሉ | 91.0 | 90.7 | 94.2 | **91.6** | 96.9 |
| | በከፊል | 4.0 | 6.7 | 1.4 | **4.9** | 1.0 |
| | አልረካሁም | 5.0 | 2.7 | 4.3 | **3.5** | 2.0 |
| የህዝብ የእጅ ቧንቧዎች | ሙሉ በሙሉ | 80.1 | | 86.2 | **77.0** | |
| | በከፊል | 5.9 | 50.0 | 6.9 | **8.8** | |
| | አልረካሁም | 14.0 | 50.0 | 6.9 | **14.2** | |
| ቦርሆሎች | ሙሉ በሙሉ | | | | **0.0** | |
| | በከፊል | | | | **0.0** | |
| | አልረካሁም | 100.0 | | | **100.0** | |
| ከውሃ ሻጭ ነጋዴዎች የተገዛ | ሙሉ በሙሉ | | 100.0 | 100.0 | **100.0** | 89.5 |
| | በከፊል | | | | **0.0** | 5.7 |
| | አልረካሁም | | | | **0.0** | 4.8 |
| የቤት ውስጥ ቧንቧዎች | ሙሉ በሙሉ | | 100.0 | 100.0 | **100.0** | 96.2 |
| | በከፊል | | | 0.0 | **0.0** | 2.8 |
| | አልረካሁም | | | 0.0 | **0.0** | 0.9 |

## ሰንጠረዥ 4፦ ዜጎች በመንግስት የጤና አገልግሎት ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ በየክልሎች ሲታይ

(ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)

| የ[illegible]ሃ ምንጭ | የእርካታ ደረጃ | ትግራይ | ኦሮሚያ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ገጠር ጠቅላላ (ድምር) | ድሬዳዋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አገልግሎት ለማግኘት የሚፈጀው ጊዜ | ሙሉ በሙሉ | 78.5 | 53.8 | 57.3 | 56.7 | 62.8 |
| | በከፊል | 11.0 | 36.3 | 23.6 | 35.8 | 22.2 |
| | አልረካሁም | 10.5 | 9.9 | 19.1 | 11.8 | 15.0 |
| የጤና ሰራተኞች/ዶክተሮች ስነ-ምግባር | ሙሉ በሙሉ | 79.5 | 55.5 | 57.7 | 58.1 | 59.9 |
| | በከፊል | 9.1 | 35.2 | 23.2 | 30.4 | 27.1 |
| | አልረካሁም | 11.4 | 9.3 | 19.1 | 11.5 | 13.0 |
| የጤና ሰራተኞች ድጋፍ | ሙሉ በሙሉ | 67.3 | 53.0 | 67.1 | 57.0 | 59.5 |
| | በከፊል | 22.4 | 36.7 | 26.4 | 33.5 | 24.7 |
| | አልረካሁም | 10.3 | 10.3 | 6.5 | 9.5 | 15.8 |
| አጠቃላይ እርካታ | ሙሉ በሙሉ | 54.2 | 49.6 | 46.4 | 49.3 | 46.6 |
| | በከፊል | 31.3 | 34.8 | 33.7 | 34.3 | 12.9 |
| | አልረካሁም | 14.5 | 15.6 | 19.9 | 16.4 | 40.5 |
| ዝቅተኛው(ቁ.) | | 419 | 506 | 246 | 1171 | 247 |

ቁ.= የተጠያቂዎች መልስ ጠቅላላ ድምር

**ሰንጠረዥ 5፦ ዜጎች በንፅህና አገልግሎት ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ**

*( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)*

| | ትግራይ | ኦሮሚያ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ገጠር ጠቅላላ(ድምር) | ድሬዳዋ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ሙሉ በሙሉ** | 57.6 | 45.0 | 44.8 | **46.7** | 25.8 |
| **በከፊል** | 25.6 | 21.6 | 23.3 | **22.6** | 13.9 |
| **አልረካሁም** | 16.8 | 33.4 | 31.9 | **30.7** | 60.3 |
| **ቁ.** | 833 | 569 | 417 | **1819** | 589 |

**ቁ.**= የተጠያቂዎች መልስ ጠቅላላ ድምር

## ሰንጠረዥ ፦ ዜጎች በትምህርት ቤቶች አገልግሎት ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ

( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)

| | | ትግራይ | ኦሮሚያ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ገጠር ጠቅላላ(ድምር) | ድሬዳዋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **የትምህርት ጥራት** | ሙሉ በሙሉ | 86.5 | 67.8 | 75.3 | 69.6 | 76.0 |
| | በከፊል | 11.1 | 27.1 | 19.7 | 25.4 | 11.6 |
| | አልረካሁም | 2.4 | 5.1 | 5.0 | 5.0 | 12.4 |
| **የትምህርት ቤት ሕንፃ** | ሙሉ በሙሉ | 67.5 | 51.2 | 58.4 | 53.9 | 80.4 |
| | በከፊል | 23.1 | 23.9 | 20.0 | 23.2 | 9.6 |
| | አልረካሁም | 9.4 | 24.9 | 21.6 | 23.0 | 10.0 |
| **ምፅዳጃ ቤት** | ሙሉ በሙሉ | 49.2 | 58.3 | 75.3 | 60.5 | 69.2 |
| | በከፊል | 13.7 | 29.9 | 14.7 | 25.7 | 12.4 |
| | አልረካሁም | 37.8 | 11.9 | 10.0 | 13.8 | 18.4 |
| **የመምህራን ስነ-ምግባር** | ሙሉ በሙሉ | 90.4 | 70.6 | 78.1 | 73.0 | 73.2 |
| | በከፊል | 8.0 | 25.1 | 16.3 | 22.4 | 16.0 |
| | አልረካሁም | 1.7 | 4.4 | 5.6 | 4.6 | 10.8 |
| **ጥቅል የእርካታ ሁኔታ** | ሙሉ በሙሉ | 41.2 | 59.3 | 55.6 | 53.9 | 71.6 |
| | በከፊል | 53.3 | 35.2 | 41.3 | 36.2 | 13.6 |
| | አልረካሁም | 5.5 | 5.4 | 3.1 | 4.8 | 14.8 |
| **ቁ.** | | **415** | **690** | **320** | **1425** | **250** |

**ቁ.**= የተጠያቂዎች መልስ ጠቅላላ ድምር

## ሰንጠረዥ 7፦ ዜጎች በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ

(ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)

| | ቁጥር | ሁሉ በሙሉ | በከፊል | አልረካሁም |
|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 835 | 41.6 | 40.4 | 18.0 |
| ኦሮሚያ | 1187 | 24.3 | 30.7 | 44.9 |
| ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | 584 | 7.9 | 26.2 | 65.9 |
| **ገጠር ጠቅላላ(ቁ.)** | **2957** | **22.3** | **30.6** | **47.1** |

**ቁ.**= የተጠያቂዎች መልስ ጠቅላላ ድምር

**ሰንጠረዥ ፰- ዘርፎች በክልል ሲለኩ: የአጠቃላይ ድምር ውጤት**

( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)

| ዘርፎች/የልኬት ውጤት | ትግራይ | ደረጃ | ኦሮሚያ | ደረጃ | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል | ደረጃ | የገጠር ጠቅላላ (ድምር) ደረጃ | የዘርፎች አጠቃላይ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የመጠጥ ውሃ** | 54.0 | 4 | 51.2 | 4 | 38.4 | 4 | 47.3 | **4** |
| **ጤና** | 65.5 | 3 | 55.5 | 3 | 58.0 | 2 | 57.4 | **3** |
| **ትምህርት** | 72.0 | 2 | 76.6 | 1 | 73.5 | 1 | 75.4 | **1** |
| **የግብርና ኤክስቴንሽን** | 78.0 | 1 | 66.8 | 2 | 51.6 | 3 | 63.0 | **2** |

**ሰንጠረዥ ፱ ክልሎች በየዘርፉ ሲለኩ፡ የአጠቃላይ ድምር ውጤት** *( ሁሉም ቁጥሮች በመቶኛ/ፐርሰንት/ ታስበው)*

| ክልሎች/የልኬት ውጤት | የመጠጥ ውሃ | ደረጃ | ጤና | ደረጃ | ትምህርት | ደረጃ | የግብርና ኤክስቴንሽን | ደረጃ | የገጠር ጠቅላላ (ድምር) ደረጃ | ደረጃ የክልሎች አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ትግራይ** | 54.0 | 1 | 65.5 | 1 | 72.0 | 3 | 78.0 | 1 | 6.0 | **1** |
| **ኦሮሚያ** | 51.2 | 2 | 55.5 | 3 | 76.6 | 1 | 66.8 | 2 | 8.0 | **2** |
| **ደ/ብ/ብ/ሕ ክልል** | 38.4 | 3 | 58.0 | 2 | 73.5 | 2 | 51.6 | 3 | 10.0 | **3** |

# ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኢን ኢትዮጵያ (ፓአኔኢ)

ፖቨርቲ አክሽን ኔትርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኢን ኢትዮጵያ (ፓአኔኢ) በኢትዮጲያ ቁጥራቸው ከ70 በላይ የሚሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች(CSOs) ጥምረት ሲሆን ድህነትን ለመቀነስ በሚነደፉ የፖሊሲ ጉዳዮች ጉልህና ተጨባጭ አስተዋፅኦ በማድረግ በተለይም የኢትዮጲያ መንግስት የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድና የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ዙሪያ በንቃት በመሳተፍ ለፍሬ እንዲበቁ በማገዝ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ሀገራዊና አለማቀፋዊ የልማት ግቦች ዳር ለማድረስም በዋነኛነት ጥናትን መሰረት ያደረጉ የፖሊሲ ትንተናች፣ለውጥ-ተኮር ቅስቀሳና የመረጃ ልውውጥ ያካሂዳል፡፡ ድርጅቱ መብት-ተኮር ልማታዊ ብሂልን በመከተል ዜጎች የአሁንም ሆነ የወደፊት እጣፈንታቸውን መወሰን እንዲችሉ በተለያዩ የልማት እቅዶች ዝግጅት፣ አፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ሂደት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና የድሆች ድምፅ ለፖሊሲ አውጪች እንዲሰሙና መንግስትም ሆነ በየደረጃው የሚገኙ ሲቪል ማህበራትና ለጋሾች ለድሆች ተጠያቂ ሆነው የማየትን ራዕይ ሰንቋል፡፡

የጥምረቱ አባላት ፈርጀ-ብዙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ያካተተ ሲሆን ሃገር በቀልና አለም-ዓቀፍ ረድኤት ድርጅቶች፣ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥምረት፣ መካነ ጥናት ተቋማት፣ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች፣ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት እንዲሁም ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች እና ሌሎች መሰል ማህበራዊ ተቋማቶችን አካቷል፡፡ አኔኢ ተልዕኮውን የማስፈፀሙና መሰል እቅድን ያነገቡ ክልላዊ አካላትን አቋቁሟል፡፡

ፓአኔኢ የተጠነሰሰው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት በኢትዮጲያ ትኩረትን በሳበበትና የተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰነዱ ዝግጅት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚችሉበት አጋጣሚ በተፈጠረበት ወቅት የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የድህነት ቅነሳ ግብረ-ኃይል እ.አ.አ 2001 ዓ.ም መቋቋምን ተከትሎ ነበር፡፡ ይኸው አዲስ ግብረ-ኃይልም በርካታ አባላትን እያቀፈ በመሄዱ የተጣለበትን ሃላፊነት በብቃት ለመወጣት ብሎም አባላቱ በድህነት ቅነሳ ስልት ረቂቅ ሰነዱ ላይ የጎላ ድርሻ እንዲኖራቸው በማሰብ ግብረ-ኃይሉን እንደ አዲስ በማቋቋም የአባል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶቹ ጥምረት ማለትም አኔኢ ለመሆን በቃ፡፡ ፓአኔኢ በእስከአሁን እንቅስቃሴው ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የድህነት ቅነሳ ስልቱን በመተግበርና የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦችን እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ በማሳተፍ ረገድ አመርቂ ውጤትን አስመዝግቧል፡፡ የድህነት ቅነሳ ስልቱን የመጀመሪያ ምዕራፍ ትግበራን በተመለከተም ለዓመታዊ የትግበራ ሁኔታ ሪፖረት ገንቢ አስተያየት ምላሽ በመስጠት እንዲሁም ሁለተኛ ምዕራፍ በሆነውና ለቀጣይ አምስት ዓመታት በሚተገበረው ድህነትን ለማስወገድ የፈጣንና ዘላቂ ልማት እቅድ(ድማፈዘልዕ) ሰነድ ዝግጅት ወቅት ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በንቃት እንዲሳተፉና የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ አድርጓል፡፡ በቀጣይነትም በእቅድ ሰነዶቹ አፈፃፀምና ክትትል እንዲሁም የግምገማ ሂደት ውስጥ አባላቱ በንቃት እንዲሳተፉ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ፓአኔኢ በአይነቱ ለሀገሪቱ አዲስ የሆነውን የዜጎች አስተያየት መሰብሰቢያ ካርድ የዳሰሳ ጥናትን(ዜአካ) በሙከራነት አካሄዶ ቀዳሚና ገንቢ የሆነ አስተዋፅኦን በማድረግ ለድህነት ቅነሳው ስልት ሰነድ ትግበራ ሂደት አጋዥ እንዲሆን ሁኔታችን አመቻችቷል፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ ቁልፍ በሆኑ ፖሊሲችና ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ተጠቃሚች (ዜጎች) ያላቸውን አመለካከት ስርዓት ባለው መልኩ የሚቀርቡበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡ ይህም ተጨባጭ የሆነና ከታች ወደላይ የሆነን ስልት በመከተል በአቅርቦትና ተጠቃሚነት ረገድ የሚወሰዱ የለውጥ እርምጃችን በተመለከተ መረጃን በመሰብሰብ ብሎም ለፖሊሲ አውጪች በተግባር የሚስተዋሉ የአቅርቦት ችግሮችን በማመላከት የአገልግሎቶቹ ጥራትና በቂነት እንዲሁም የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞችን

ውጤታማነት ለመለካት የሚያስችል መንገድን ይፈጥራል፡፡ አኤኢ የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ በድማፊዘልዕ ሰነድ ዝግጅት ወቅት አስተያየቶችን ለመንግስት ሰጥቷል፡፡ ይህ የመጀመሪ ደረጃ ጥናትም ገንቢና ጠንካራ የሆኑ መረጃች የሚሰበሰቡበትን ስልቶች በማመላከት ለድማፊዘልዕ ትግበራ ስኬታማነት አስተዋፅኦ ያደርጋል ብለን እናምናለን፡፡